

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

“ወፌ ቆመች” ተከታታይ የሬድዮ ድራማ ከሬድዮ ድራማ አላባዊያን አንጻር

በ

ናፊያድ ሸፈራው

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ነሃሴ 2013 ዓ.ም

“ወፌ ቆመች” ተከታታይ የሬድዮ ድራማ ከሬድዮ ድራማ አላባዊያን አንጻር

በ

ናፊያድ ሽፈራው

የጥናቱ አማካሪ

መ/ርት ዳናይት ብርሃኑ

ለአርትስ አፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ነሃሴ 2013 ዓ.ም

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማመከሪያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም.....ፊርማ.....

ይህ በተማሪ **ናፊያድ ሸፈራው የወፌ ቆመች የራድዮ ድራማ ከራድዮ ድራማ አላባዊያን አንጻር** በሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥንታዊ ፅሑፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት ደረጃ ያሟላ እና ለቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጣል።

ፈታኝ1 ፊርማ

....

ፈታኝ2 ፊርማ

....

ቀን.....

ምስጋና

ከሁሉ በፊት የሆነው ሁሉ እንዲሆን ለፈቀደው ለድንግል ማሪያም ልጅ አማኑኤል ክብር እና ምስጋና ይግባው።በመቀጠል ለመኖሬ ምክንያት ለሆነው በህይወቴ ሁሉ ድጋፍ ሆኖ ለዚህ ላደረሰኝ የህይወት አማካሪዬ አባቴ ሽፈራው ነጋሽ ምስጋናዬ ከልብ ነው።እንዲሁም ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ስሰራ በማማከር፣ በማበርታት፣በማገዝ ከጎኔ ያልተለያችሁኝ የሁልጊዜ ጓደኞቼ ዮርዲ፣ሱራ፣አብሲ ይህን ጥናት ስሰራ ላገዛችሁኝ ከጎኔ ለነበራችሁ የክፍል ተማሪዎች ሌሎችም ጓደኞቼ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።በተጨማሪ መረጃ በመስጠት የተባበራቹኝ ፣በማበርታት አይዞሽ ያላቹኝ መምህራኖቼ አመሰግናለሁ።በመጨረሻም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ፀባዬን ችላ፣ታግሳ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ እዚህ እንዲደርስ ለረዳቸኝ፣ አማካሪዬ መምህርት ዳናይት ብርሃኑ ምስጋናዬ ይድረስ።

አበርክቶ

ህይወቱን ሙሉ ለእኔ ለኖረው ሳይኖር ላኖረኝ ለህይወት መምህሬ ለውድ አባቴ ይሁንልኝ።አባ እወድሃለው።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የ"ወፈ ቆመች" ተከታታይ የራዲዮ ድራማ ከራዲዮ ድራማ አላባዊያን አንፃር በሚል ርዕስ የቀረበ ነው።ጥናቱ የሚያተኩረው ወፈቆመች የራዲዮ ድራማን ከራዲዮ አላባዊያን አንፃር መተንተን ላይ ሲሆን ከሰው ድምፅ ከሙዚቃ፣ከዝምታ እና ከግብአተ ድምፅ አንፃር የሚተነትን ነው።አጥኚዋ ጥናታዊ ፅሁፉን ሰርታ ለማጠናቀቅ መዛግብትን በማንበብ፣ቃለ መጠይቆችን በማድረግ በተገኘው መረጃ መሰረት የወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማን ከራዲዮ አላባዊያን አንፃር በመተንተን የወፈ ቆመች የሬድዮ ድራማን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ማግኘት ችላለች።

ማውጫ

ምስጋና ..... **IV**

አበርክቶ ..... **V**

አጠቃሎ ..... **VI**

ምዕራፍ አንድ **1**

1.መግቢያ **1**

1.2 የጥናቱ አላማ 2

1.2.1 የጥናቱ ዐብይ አላም 2

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ 2

1.4 የጥናቱ መጠነ ርዕይ 3

1.5 የጥናቱ ዘዴ 3

1.5.1 የጥናቱ ኣይነት *3*

1.6 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች 3

1.7 የጥናቱ አወቃቀር 4

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 4

1.8.1.የመፍትሔ ሀሳብ 4

ምዕራፍ ሁለት **5**

2.የተዛማጅ ጹሁፎች ቅኝት እና ንድፈ ሀሣባዊ ቅኝት **5**

2.1. የራዲዮ ምንነት? 5

2.2. የራዲዮ አጀማመር 5

2.3.የራዲዮ ድራማ ምንነት 6

2.5.የራዲዮ ድራማ መዋቅሮች 6

2.6. የራዲዮ ድራማ ጽህፈ ተውኔት አላባዊያን 7

2.6.1 ገፀ-ባህሪያት 8

2.6.2.መቼት 8
2.6.3 ቃለ ተውኔት 9
2.6.4. ድርጊት 10
2.6.5 ልብ ሰቀላ 10
2.6.6. ሴራ 10
2.6.7.ግብአተ-ድምፅ 11
2.6.8 ተራኪ 12
2.7. የራዲዮ ድራማ አላባዊያን 12
2.7.1. የሰው ድምፅ 12
2.7.2.ሙዚቃ 13
2.7.3.ዝምታ (ፀጥታ) 13
2.7.4.ግብአተ ድምፅ 14
2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 14
ምዕራፍ ሦስት 15
3.የመረጃ ትንተና 15
3.1 የወፌ ቆሞች ደራሲ እና አዘጋጅ ቀደምት ሰራዎች 15
3.2የወፌ ቆሞች ራዲዮ ድራማ ባለሙያዎች 16
3.3የወፌ ቆሞች የራዲዮ ድራማ ታሪክ 17
3.4 . "ወፌ ቆሞች"የራዲዮ ድራማ ከአላባዊያን አንጻር 18
3.4.1."ወፌ ቆሞች"የራዲዮ ድራማ ከሙዚቃ አጠቃቀም አንፃር 18
3.4.1.1.ሙዚቃ ከገፀ-ባህሪ አንፃር 18
3.4.1.2.ሙዚቃ ከታሪክ አንፃር 19
3.4.1.3ሙዚቃ ከመቼት አንፃር 19
3.4.2 ወፌ ቆሞች የራዲዮ ድራማ ከግብአተ ድምፅ (sound effect) አንፃር 20
3.4.2.1ግብአተ ድምፅ ከገፀ ባህሪ አንፃር 20
3.4.2.2.ግብአተ ድምፅ ከመቼት አንፃር 21
3.4.2.3ግብአተ ድምፅ ከታሪክ አንፃር 22
3.4.3 ወፌ ቆሞች ከሰው ድምፅ አንፃር 23
3.4.3.1የሰው ድምፅ ከገፀባህሪ አንፃር 24
3.4.3.2የሰው ድምፅ ከመቼት አንፃር 25
3.4.3.3የሰው ድምፅ ከታሪክ አንፃር 26
3.5. ወፌ ቆሞች የራዲዮ ድራማ ከዝምታ አንፃር 27
4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ 29
4.2 የመፍትሔ ሀሳብ 31

ጥቅሶች በመግኛ ቋንቋቸው .....
ዋቢ መፅሃፍት .....

ምዕራፍ አንድ

1.መግቢያ

የራዲዮ ድራማ የአንድን ማህበረሰብ ወግ፣እምነት፣የኑሮ ደረጃ፣የመሳሰሉትን እንድናውቅ የሚረዳን ጥበብ ነው።የማዳመጥ ጥበብ የሆነው ራዲዮ ድራማ የተለያዩ ገፀባህሪያትን በመቅረፅ፣በጆሮ የሚደመጥ በአህምሮ ምስልን የሚከስት ጥበብ ነው። በተጨማሪም ራዲዮ ድራማ ተግባራዊ እንቅስቃሴን፣ምስልን ሳይጨምር በድምፅ ግብአቶች ብቻ ለአድማጭ በሚያዝና እና በሚያስተምር መልኩ የሚቀርብ ነው።

የራዲዮ ጥበብ ከጥንት ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ለሰው ልጅ ትልቅ ጠቀሜታን እየሰጠ ይገኛል።በሀገራችን የራዲዮ አጀማመር ስንመለከት በርካታ ፅሁፎች፣ጥናቶች እና መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ለሀገራችን የራዲዮ ቴክኖሎጂ እድገት የ1933 የጣሊያን ወረራ ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳደረገ ይገልፃሉ።ቀደም ባሉት ዐመታት አዋጆች፣ቅስቀሳዎች ሲነገሩ በጣም አድካሚ በሆነ እና ኃላ ቀር በሆነ መልኩ እንደነበረ ይታወሳል።በኃላም በጣሊያን ወረራ ወቅት ጣሊያኖች ባመጡት ዘመናዊ መሳሪያ አማካኝነት የራዲዮ ቴክኖሎጂ እንደተጀመረ ይነገራል።በጣሊያን ወረራ ወቅት የተለመደ መደበኛ ፕሮግራም ቀርቦ አያውቅም። ይጠቀሙበት የነበረው ለቅስቀሳ እና ለፕሮፓጋንዳ ሲሆን አገልግሎቱም በኢ.አ ብቻ ነበር።

በሀገራችን ቴክኖሎጂ ከገባበት ዘመን እስከ አሁን ድረስ በቁጥር እንዲህ ነው ተብለው የማይገለፁ በርካታ የራዲዮ ድራማዎች ተሰርተዋል።ከእነዚህም ውስጥ "ወፌቆመች"አንዱና ተጠቃሽ ነው።ወፌ ቆመች በመህዛ ወርቁ ተፅፎ ለአድማጭ የበቃ ስራ ነው። ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ በሸገር ኤፍ.ኤም 102.1 በሳምንት አንድ ቀን የሚቀርብ ተከታታይ የራዲዮ ድራማ ነው።ወፌ ቆመች በየሳምንቱ አዳዲስ ርዕሰ ጉዳዮችን ይዞ በመቅረብ "የቅዳሜ ጭዋታ" በተሰኘ ፕሮግራም ላይ ከ፡30 የሚቀርብ ሲሆን የድራማው አይነት በሁነቶች ላይ ያተኮረ አስቂኝ የቤተሰብ የራዲዮ ድራማ ነው።ይህ ጥናትም ማንኛውም የራዲዮ ድራማ ማሟላት ያለበትን አላባዊያን አሟልቶ እንደሚሰራ ሁሉ ወፌ ቆመችም እነዚህን አላባዊያን ማለትም የሰው ድምጽ፣ ሙዚቃ፣ዝምታ፣ግብዐተ ድምጽን በምን መልኩ ተጠቅሟል?የሚለዉን እንዲሁም አላባውያኑን በጥልቀት መተንተን ላይ ያተኩራል።

1.1 የጥናቱ ዳራ

አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማጥናት ያነሳሳት በራዲዮ ድራማ ላይ የተሰራ በቂ ጥናታዊ ፅሁፍ ባለማግኘቷ እና በራዲዮ ድራማ ጥበብ ላይ የራሷን አስተዋፅዖ ለማበርከት ካላት ጥልቅ ፍላጎት የተነሳ ነው።እንዲሁም

ወፈቆመች የራዲዮ ድራማ በሀገራችን ከተሰሩ የራዲዮ ድራማዎች ታዋቂ እና የማህበረሰቡን ችግር ያመላከተ ጭብጥ የያዘ መሆኑ ስለታያት ሌሎች በዚህ ዘመን እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በዚህ መልኩ ቢሰሩ የሀገራችን የጥበብ ዘርፍ ምን ያህል ወደፊት መራመድ እንደሚችል በማሰብ ይህን የራዲዮ ድራማ በጥልቀት ለመተንተን ካደረባት ከፍተኛ ፍላጎት በመነሳት ነው።

1.2 የጥናቱ አላማ

1.2.1 የጥናቱ ዐብይ አላም

የዚህ ጥናት ዐብይ አላማ ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማን ከራዲዮ ድራማ አላባዊያን አንጻር መተንተን ነው።

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማን ከሰው ድምጽ አጠቃቀም አንጻር መመልከት።

ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማን የሙዚቃ አጠቃቀም በጥልቀት መቃኘት።

ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማን ከግብዐተ ድምጽ አጠቃቀም አንጻር መተንተን።

ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማን የዝምታ አጠቃቀም በጥልቀት መመልከት ነው።

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

የወፈ ቆመች የሰው ድምጽ፣ዝምታ፣ግብዐተ ድምጽ፣ሙዚቃን በጥልቀት ለመረዳት ይጠቅማል።

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ማህበረሰቡ ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የታዩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን እንዲለይ ያደርጋል።

በራዲዮ ድራማ ላይ ለሚሰሩት ጥናቶች እንደ ማጣቀሻነት ይረዳል።

1.4 የጥናቱ መጠነ ርዕይ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ወፌቆመች ራዲዮ ድራማን ማለትም በምህራፍ አንድ፡-ክፍል1፣2፣3፣12 ከምህራፍ ሁለት፡-ክፍል 13፣14፣15፣16፣26 ከምህራፍ ሶስት፡-ክፍል 27፣28፣29፣30፣37 በመውሰድ ሬዲዮ አላባዊያ አንፃር የሚተነትን ሲሆን ይህም የሰው ድምጽን፣ሙዚቃ፣ዝምታ፣ግብዐተ ድምጽ ላይ የተወሰነ ነው።

1.5 የጥናቱ ዘዴ

1.5.1 የጥናቱ አይነት

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ገላጭ ከሚባለው የጥናታዊ ጽሁፍ አይነት ይመደባል።ያለው እንዳውቅ "የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር"(2009፣21) በሚለው መጽሃፍ ውስጥ ስለገላጭ ምርምር እንዲህ ሲል ያትያል"ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተው አንድ ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምንያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርቡበት ነው። አጥኚዋ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ በምታዘጋጅበት ጊዜ ብዙ ዘዴዎችን ትጠቀማለች።በዋነኛነት በማዳመጥ ሲሆን ወፌ ቆመች የተሰኘውን ራድዮ ድራማ በተደጋጋሚ በማዳመጥ፣ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና ሌሎች ስለ አላባዊያን የተጻፉ ጽሁፎችን በመዳሰስ ይሆናል።

1.6 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የሰው ድምፅ አጠቃቀም ምን ይመስላል?

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ ሙዚቃን እንዴት ተጠቅመዋል?ምን ጠንካራ ና ደካማ ጎኖች አሉት?

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የግብአተ ድምፅ አጠቃቀም በምን መልኩ ነው?ጠንካራና ደካማ ጎኖቹ ምን ምን ናቸው?

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ ዝምታ አጠቃቀም በምን መልኩ ይቃኛል።

ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የተጠቀሚቸው የራዲዮ አላባዊያን ታሪክን፣ገፀ ባህሪን፣መቼትን፣በምን መልኩ ገልፀዋል?

1.7 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በምዕራፍ አንድ፡-የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አላማ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ዘዴ፣ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣የጥናቱ አወቃቀር፣በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳብ የሚሉትን ያካትታል። በምዕራፍ ሀለት፡-የተዛማች ስራዎች ቅኝት፣የራዲዮ ድራማ ምንነት፣የራዲዮ ድራማ አጀማመር፣የራዲዮ ድራማ መዋቅሮች፣የአላባዊያን ምንነት፣የራዲዮ ድራማ ስክሪፕት አላባዊያን፣ የራዲዮ ድራማ የአላባዊያን ይዟል። በምዕራፍ ሦስት፡- የመረጃ ትንተና የራዲዮ ድራማ ታሪክ፣ወፈ ቆመች ከሙዚቃ አንጻር፣ወፈ ቆመች ከግብዐተ ድምጽ አንጻር፣ወፈ ቆመች ከሰው ድምጽ አንጻር፣ወፈ ቆመች ከዝምታ አንጻር የሚሉትን ይይዛል። በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ፣የመፍትሄ ሀሳብ፣ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው እና ዋቢ መፅሐፍትን ይይዛል።

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በምታዘጋጅበት ጊዜ የመረጃ እጥረት ማለትም ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ማጣቀሻነት ጉልህ ሚና ያላቸው መፅሐፍትን በበቂ ሁኔታ አለማግኘቷ፣ጥናታዊ ፅሑፉን በተገቢው መልኩ ሰርቶ ለማጠናቀቅ መረጃዎችን ለመስጠት ፣ለማማከር እና ለትብብር ፍቃደኛ የሆኑ ግለሰቦች እና ተቋማት አለማግኘት፣በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የቀደምት ጥናቶችን አለማግኘት አጥኚዋ የአጋጠሟት ችግሮች ናቸው።

1.8.1.የመፍትሔ ሀሳብ

አጥኚዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ሰርታ ለማጠናቀቅ ላጋጠሟት ችግሮች መፍትሄ አድርጋ የወሰደችው ለትብብር ፍቃደኛ ያልሆኑ አካላትን ታግሶ መጠበቅ፣በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መፅሀፍትን በበቂ ሁኔታ ባለማግኘቷ በሌላ ቋንቋ የተፃፉ መፅሀፍትን በማንበብና በመተርጎም እንዲሁም ስለ ራዲዮ የተፃፉ ባይሆኑም ተቀራራቢነት ያላቸው መፅሀፍትን በመዳሰስ፣በቀጥታ ባይሆንም በተዘዋዋሪ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው የቀደምት ጥናቶችን በመጠቀም ጥናቱን በተሟላ መልኩ ለመጨረስ ችላለች።

ምዕራፍ ሁለት

2.የተዛማጅ ጹሁፎች ቅኝት እና የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

2.1. የራዲዮ ምንነት?

ራዲዮ እንደ ቴሌቪዥን በምስል የሚቀርብ ና በአይን የሚታይ ሳይሆን በጆሮ የሚደመጥ የመዝናኛ እና የማስተማሪያ ሚዲያ ነው።ራዲዮ በማንኛውም ቦታ ምንም አይነት ክንውኖችን እያካሄድን ማዳመጥ የምንችለው ሚዲያ ነው።ይህ ጥበብ ብዙ ወጪን የማይጠይቅ በገጠርም በከተማም በቀላሉ ተደራሽ መሆን የሚችል ነው።ራዲዮ ድምፅን በመጠቀም መልዕክትን ለአድማጭ ማስተላለፊያ መሳሪያ ነው።ይህም ሒደት የሚከናወነው በኤሌክትሪክ ሞገድ አማካኝነት ድምፅን በማስተላለፍ ነው።oberiri Destiny Apuke Introduction to Radio Productionበተሰኘ መፃህፉ እንዲህ አስቀምጧል "እንደ Idebi(2008:1) አገላለፅ ራዲዮ የሚለው ቃል የሚያመላክተው ሞገዶችን በመጠቀም መልዕክትን በአየር ላይ የመላክ እና የመቀበል ሒደት ነው ይላል።"[1](2017, 8) በተጨማሪም የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን ለአድማጭ የማስተላለፍ ወይም የማድረስ ሂደት ነው።በራዲዮ የተለያዩ ፕሮግራሞች ይቀርባሉ ከነዚህም መካከል ዜናዎች፣የተለያዩ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች፣የውይይት ፕሮግራሞች፣ትምርታዊ እና አዝናኝ የልጆች ፕሮግራሞች፣ድራማዎች...እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው።አጥኚዋ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ትኩረቷ የራዲዮ ድራማ በመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ምሳሌዎች የራዲዮ ድራማን በሰፊው ለመዳሰስ ሞክራለች።

2.2. የራዲዮ አጀማመር

የራዲዮ አጀማመር ስንመለከት በ1842 Samuel Morse የመጀመሪያውን የድምፅ ማስተላለፊያ እንደፈጠረ ምሁራን ይናገራሉ።ይህን ሀሳብ ለመደገፍ oberiri Destiny Apuk" Introduction to Radio production" በተሰኘ መፅሀፉ ይህን ያስቀምጣል::

> የራዲዮ ታሪክን ስንመለከት ወደ 19ኛው ክፍለ ዘመን ተመልሰን የsamuel morsenን የኤሌክትሪክ ቴሌግራፊ ግኝት ማንሳት ይገባናል።እንደ Bittner አገላለፅ(1983:93)(Gulgielmo marconi) ገመድ አልባ የሆነ የድምፅ ማስተላለፊያ electromagnetic መፍጠሩን ነው። እነዚህም ግኝቶች ድምፅን በርቀት ማስተላለፍ የቻሉ ነበሩ።ይሄም በ1866 የድምፅ ስርጭት ከእንግሊዝ ተነስቶ እስከ አሜሪካ ድረስ ያለ ገመድ ዝርጋታ የተላለፈ ነበር።

sambe(2008:75)እንደሚያስቀምጠው በ1988 Henirick Hertz በእንግሊዙ ተመራማሪ በclark maxwell የ electromagneti ጥናት በመነሳት ለመጀመሪያ ጊዜ የራዲዮ ሞገድን ፈጥሯል።[2]

2.3.የራዲዮ ድራማ ምንነት

የራዲዮ ድራማ እንደማንኛውም የድራማ ስክሪፕት አፃፃፍ ሁሉ ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ የሚያነሳ እና መጀመሪያ፣መሀከል፣እና መጨረሻ ያለው ነዉ።ፋንታሁን እንግዳ የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ በተሰኘ መፅሐፉ ውስጥ የራዲዮ ድራማ በዚህ መልኩ አብራርቶ አስቀምጦታል።" የራዲዮ ተውኔት ሙሉ በሙሉ በድምፅ ብቻ የሚሰራጭ ትርዒት በመሆኑ ጆሮ ግቡ ተውኔት እየተባለ ይጠራል። የራዲዮ ድራማ በገፀ-ባህሪያቱ፣በቃለ-ተውኔቱ፣በታሪኩ፣በቋንቋው ለአድማጭ ግልፅ እና ግርታን የማይፈጥር መሆን ይኖርበታል።"(2009 ዓ.ም -ገጽ 100)ታሪክን በተመለከተ ግን የራዲዮ ድራማ ለየት ይላል።የራዲዮ ድራማ በአይን የማይታይ/non visual/ በመሆኑ ውስብስብ ድርጊት ያልበዛበት ቀላል ታሪክ ሊኖረው ይገባል። "ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ_ቃላት እና ብያኔዎቻቸው በሚለው መፅሀፉ ውስጥ እንደገለፀው

> የራዲዮ ተውኔት በቂ አድማጭ እንዲኖረው ከተፈለገ በሴራ አወቃቀሩ፣በገፀ-ባህሪያት አሳሳል እና በቋንቋ አጠቃቀሙ የአድማጭን ተውኔት ተመልካች ሙሉ ጊዜን ሰውቶ ስራዬ ብሎ ሳይሆን የሚከታተለው አንድ አይነት ተግባር እያከናወነ ወይም በመንገድ እየተጓዘ ካለዚያም አልጋ ላይ ጋደም ብሎ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም የሚተላለፈው ተውኔት ተደራሲው ከያዘው ተደራቢ ስራ በበለጠ ማራኪ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል።ታሪኩ ማራኪ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ፣ ዝግጅቱም የተዋጣለት እስከሆነ ድረስ የራዲዮ ተውኔት አድማጭ በቁጥር አቻ አይገኝለትም።(1993፣89)

2.5.የራዲዮ ድራማ መዋቅሮች

2.5.1.መቅድመ ታሪክ/PROLOGUE/፡-ትዕይንቱ ከመጀመሩ በፊት ስለ ድራማው አንዳንድ ጉዳዮች ርዕሰ ጉዳይ፣የድራማው ይዘት (አስቂኝ፣አሳዛኝ)፣ገፀ ባህሪያት የሚተዋወቁበት ሂደት ነው ።አስታጥቃቸው ይሁን ባዘጋጀም የመማሪያ ሞጁል ላይ እንዲህ አስቀምጦታል።" ይህ ገፀባሕርያት ና የድርጊቱ ሁኔታ

በምጥን የሚተዋወቅበት መቅድመ ትዕይንት ነው።መቅድመ ታሪክ ገፀባሕርያቱንና ክንዋኔውን ባጭር አርነ ከማቅረብ ጋር ትረካዊ ትውውቅ የሚሰጥ ነው።"(አስታጥቃቸዉ ይሁን፣ የመማሪያ ሞጁል፣1998 ዓ.ም)

2.5.2.ገቢሮች/ACTS/፦ገቢር የአንድ የጥበብ ስራ ዋና ክፍል ማለት ነው። ገቢር በተለያዩ ክፍሎች ተከፋፍሎ ይቀርባል እነዚህም ትናንሽ ክፍሎች ትዕይንት በመባል ይታወቃሉ።አስታጥቃቸው ይሁን ባዘጋጀው የመማሪያ ሞጁል እንደገለፀው፡- "የፅሁፉ ተውኔትን ጠቅላላ አካል የሚመሰርቱት ተለቅ ተለቅ ያሉ ክፍሎች ናቸው።"(አስታጥቃቸዉ ይሁን፣ የመማሪያ ሞጁል፣1998 ዓ.ም)

2.5.3.ትዕይንቶች/SCENES/፡-የአንድ ጥበብ ስራ ንዑስ ክፍሎች ትዕይንት ይባላሉ። በተውኔት ውስጥ የትዕይንት ለውጥን ለማሳወቅ መጋረጃ መክፈትና መዝጋት ወይም መብራትን በመጠቀም የትዕይንት ለውጥን ያሳያሉ።በራዲዮ ድራማ ደግሞ የትዕይንት ለውጥን ለማሳወቅ የመሸጋገሪያ ሙዚቃን ይጠቀማሉ። አስታጥቃቸው ይሁን ባዘጋጀው የመማሪያ ሞጅል ላይ ትዕይንትን እንዲህ ገልጿል። "የራዲዮ ድራማ ሁለተኛዎቹ አነስተከፍሎች/SUBUNITS/ናቸው።"(አስታጥቃቸዉ ይሁን፣ የመማሪያ ሞጁል፣1998 ዓ.ም)

2.6. የራዲዮ ድራማ ጽህፈ ተውኔት አላባዊያን

የልቦለድ ና የተውኔት አላባዊያን ተመሳሳይነት አላቸው።የራዲዮ ድራማ ግን ከሁለቱ የጥበብ ስራዎች ለየት የሚያደርገው ነገር አለ።የተወሰነ ተመሳሳይነት ቢኖረውም ነገር ግን ራዲዮ ድራማ ልቦለድ ና ተውኔት የማይጠቀሟቸውን አላባዊያን ይጠቀማል።ራዲዮ ድራማ በምስል መታየት ባለመቻሉ በአድማጭ አህምሮ ውስጥ ምስልን መከሰት የሚያስችሉ በጆሮ ሰምተን ቦታን ፣ጊዜን ማህበራዊ ሁኔታን ለመረዳት የሚጠቅሙ ከተውኔት እና ልብወለድ አላባዊያን የተለየ አላባዎችን ይጠቀማል። ፋንታሁን እንግዳ የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴዎች በተሰኘ መፅሀፉ እንደገለፀው "የራዲዮ ተውኔት አላባዎች ከሌሎች የተውኔት ዓይነቶች አላባዎች በአብዛኛው ይመሳሰላሉ።ይሁን እና ግን የራዲዮ ተውኔት ከዕይታዊ አላባዎች የማይደመሩ እና ከገፀ-ባህሪ የማይደመሩ አላባዎችን ጥቅም ላይ ያውላል።ለምሳሌ፡-የመሸጋገሪያ ሙዚቃ፣ግባተ-ድምፅ፣ አስተናጋጅ(ለፋፊ) እና ተራኪ ከመድረክ ና ቴሌቪዠን የተውኔት ዘውጎች በተለየ መልኩ ግልጋሎት ላይ ይውላሉ።"(2009፣102)

ስለ ራዲዮ ድራማ አላባዊያን የተለያየ ሀሳብ ያላቸው ገለፃዎች አሉ። የተለያዩ ምሁራን በራዲዮ ድራማ ላይ የተለያዩ ሀሳቦችን ያስቀምጣሉ።አጥኚዋ አርትስ አንላይን በተሰኘ ድረ ገጽ ላይ እንዳገኘችው የራዲዮ ድራማ

አላባዊያን ገፀ ባህሪ፣ቃለ ተውኔት፣ድርጊት፣መቼት እና ልብ ሰቀላ ናቸው ብለው ያስቀምጣል።ዋልዶት አቦት ደግሞ Handbook of broad casting በተሰኘ መፅሀፉ ላይ የራዲዮ ድራማ አላባዊያን ገፀ ባህሪ፣ ሴራ፣ቃለ ተውኔት፣ሳውንድ ኢፌክት፣ትረካ ናቸው ብሎ ያስቀምጣል። ሩቤን ቤርሚጆ ደግሞ የሬድዮ ድራማ የሰው ድምጽ፣ሙዚቃ፣ዝምታ፣ግብአተ ድምጽ ናቸው ብሎ በአራት ይከፍላቸዋል። ሁሉም የተለያዩ ሀሳቦችን ቢያስቀምጡም የሚጋሯቸው ሀሳቦችም አሉ።ሁሉንም ሀሳቦች በዝርዝር እንደሚከትለው እንመልከት።

2.6.1 ገፀ-ባህሪያት

በራዲዮ ድራማ ውስጥ ገጸ ባህሪያት ማለት ከታሪኩ ጋር ዝምድና ያላቸው የገሀዱ አለም ወኪሎች ሰዎች እና እንስሳት ናቸው።የራዲዮ ተውኔት ገፀ-ባህሪያት በቁጥር መብዛት የለባቸውም።አድማጭ ግራ እንዳይጋባ ገፀ ባህሪያቱ የተመጠኑ መሆን አለባቸው።ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው በሚለው መፅሀፉ ላይ እንደገለፀው "ተደራሲያን ድርሰቱን የሚከተሉት የተዋንያንን ንግግር እያዳመጡ ስለሆነ በድርሰቱ ውስጥ የሚሳሉት ገፀ ባህሪያት ቁጥር የተመጠነ እንዲሆን ይጠበቃል። "(1993፣88) የራዲዮ ድራማ በአጠቃላይ የተወሰኑ ገፀ ባህሪያቶች ናቸው የሚኖሩት።ይህም የሆነበት ምክንያት ልክ እንደ መድረክ ቲያትር ገፀ ባህሪያቱ ስለማይታዩ በተደጋጋሚ የሚያወሩ ከሆነ አድማጩ እነሱን የመርሳት ዕድል ይኖረዋል። እንዲሁም ለአድማጮች ገፀ ባህሪያቱን በድምፅ ብቻ ለመለየት ይከብዳቸዋል እናም አድማጮች ስለ አንድ ገፀ ባህሪ ለማወቅ ምን እንደሚል ወይም ደግሞ ሌሎች ስለ ገፀ ባህሪው የሚሉትን በመስማት እና ድምፃቸውን በማዳመጥ ለማወቅ(ገፀ ባህሪውን ለመለየት) ይችላሉ።

ሮበርት ሂላርድ ሬድዮ ብሮድካስቲንግ በተሰኘው መፅሀፉ ላይ ሀሳቡን በዚህ መልኩ ገልፆታል።"በራዲዮ ድራማ በርካታ ገፀ ባህሪያትን ማሳተፍ እንደሚቻል አድርጎ ማሰብ ይቻላል።ምክንያቱም በአንድ ትዕይንት ውስጥ አድማጭ መለየት የሚችለው የአራት ወይም የአምስቱን የተለያየ ድምፅ ብቻ ነው።"[3] (1950፣97)

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች ስንመለከት በአጠቃላይ በራዲዮ ድራማ ውስጥ የምንጠቀማቸው ዋና ገፀ ባህሪያት ቁጥር የተመጠነ መሆን አለበት ወደ ሚል መደምደሚያ ያደርሰናል።

2.6.2.መቼት

መቼት ማለት የሬድዮ ድራማው የተካሄደበት ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ማህበራዊ እውነታ ማለት ነው። በራዲዮ ድራማ ውስጥ የመቼት አጠቃቀማችን(አገላለፃችን) ውስን አይደለም ግብአተ ድምፅን በመጠቀም

ማንኛውንም ቦታ እና ጊዜ መፍጠር እንችላለን።በቴሌቪዥን፣ለመፍጠር ወይም ለመግለፅ ከባድ(አድካሚ) የሆኑ ቦታዎችን እና ጊዜያትን በራዲዮ ድራማ በቀላሉ በግብአተ ድምፅ አማካኝነት መፍጠር ይቻላል። በራዲዮ ድራማ ውስጥ ቦታ መረጣ እና ተዋናዮች ቦታው ድረስ ሄደው መተወን አይጠበቅባቸውም የራዲዮ ተውኔት በስቱዲዮ ውስጥ ተሰርቶ ያለ ተዋናዮች ልፋት እንዲሁም ያለምንም ድካምና ለአጉል ወጪ ሳይዳረጉ ማንኛውንም እሩቅ ስፍራ በቀላሉ መፍጠር ይቻላል።ለምሳሌ፦የበረሃ፣አየር መንገድ፣ዝናብ ያለበት ስፍራ፣ ወ.ዘ.ተ በቀላሉ መግለፅ ይቻላል። ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው በሚለው መፅሐፉ ላይ እንደገለፀው "በራዲዮ ተውኔት የሚቀረፀው የመቼት ዓይነት እንደ መድረክ ተውኔት ቁጥብነት ያለው ወይም አንድ-ነትን የጠበቀ እንዲሆን አይፈለግም።የራዲዮ ተውኔት መቼት ቶሎ ቶሎ የመለዋወጥ ሙሉ ነፃነት ስላለው የጊዜና የቦታ ለውጥን በተመለከተ በአንድ ተውኔታዊ ታሪክ ውስጥ በተፈለገው ቁጥር ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።"(1993፣ 89)

2.6.3 ቃለ ተውኔት

ቃለ ተውኔት ማለት በአንድ የሬድዮ ድራማ ስራ ውስጥ ትልቁን ሚና የሚጫወት የሬድዮ ድራማ ህይወት ልንለው የምንችለው ነው።በቃለ ተውኔት የደራሲውን የውስጣዊ ሃሳብ ለመረዳት የድርሰቱንም ታሪክ፣የገጸ ባህሪያትን ሁኔታ፣ጸባይ፣ወዘተ ለመረዳት የሚያስችለን ቃለ ተውኔት ነው።ጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ እና ሌሎች ባዘጋጁት "መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መርሆዎች "በሚለው መጽሃፍ ቃለ ተውኔትን እንዲህ ይገለጻሉ።"ቃለ ተውኔት የደራሲ አብይ የመናገሪያ ወይም የመግለጫ መሳሪያ ነው።"(2009፣77)

በራዲዮ ተውኔት ውስጥ ሁሉም አላባዊያን የሚገለፁት ማለትም ታሪኩ፣ገፀ ባህሪያቱ፣መቼቱ፣ሴራው ሁሉም የሚተዋወቁት በቃለ ተውኔት ነው።ቃለ ተውኔት በራዲዮ ድራማ ውስጥ ዋና መሳሪያ ነው። ስለዚህም በራዲዮ ድራማ ውስጥ የምንጠቀመው ቃለ ተውኔት ፀያፍ ቃላት፣የሰዋሰው ግድፈት የሌለበት እንዲሁም ከበድ ያሉ ቃላትን መጠቀም የለብንም።ፋንታሁን እንግዳ ይህን ሀሳብ እንዲህ በማለት ይደግፈዋል።"የራዲዮ ተደራሲ ቆም በሎ ለማንሰላሰል ጊዜ ስለሌለው የሚፃፍለት ጉዳይ ከፍልስፍና ነክ ከአመራማሪ እና ሙያዊ ቃላት ጋር መያያዝ የለበትም።ቃለ-ተውኔቱ የዕለት ተዕለት ንግግርን መምሰል አለበት።"(ተዉኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸዉ ፣1993፣89)

ቃለ-ተውኔት አጠቃቀማችን የራዲዮ ድራማውን ጥሩም መጥፎም የማረግ አቅም አለው።ታሪኩ ጥሩ ሆኖ ሳለ የተጠቀምናቸው ቃለ ተውኔቶች ከታሪኩ ጋር የማይሄዱ አድማጭ ማህበረሰቡን የማይወክሉ፣ ለመረዳት ከበድ ያሉ ሙያዊ ቃላትን ከሆኑ ስራችንን ሊያበላሹ ይችላሉ።ስለዚህ ቃለ ተውኔት አጠቃቀማችን በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል።

2.6.4. ድርጊት

ድርጊት በአንድ የጥበብ ስራ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለው የታሪኩ አካሄድ(ፍሰት)ማለት ነው።ይህ ማለት በታሪኩ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ወይም ድርጊትን ያካተተነው። በራዲዮ ድራማም ሆነ በመድረክ ትወና ላይ ድርጊት ምን እንደሚፈጠር የሚያሳይ ነው።ገፀ ባህሪው ላይ ምን እንደሚፈጠር፣ለተፈጠረው ነገር ምን አይነት ምላሽ እንደሚሰጥ እና ሁሉም ነገሮች እንዴት እንደሚጠናቀቁ ማብራራት ነው።ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው "በሚለው መጽሃፉ ስለ ድርጊት እንዲህ ያስቀምጣል።"ድርጊት በተውኔት ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መደምደሚያ ያለው የታሪኩ ሂደት ወይም ንቅናቄ ነው።"(1993፣104)

2.6.5 ልብ ሰቀላ

በአንድ የጥበብ ስራ ውስጥ አጓጊ ድርጊትን በመፍጠር አድማጩ በጉጉት እንዲጠብቅ ማድረግ፣በአድማጩ አህምሮ ውስጥ ማን፣መቼ፣ለምን፣እንዴት የሚሉ ጥያቄዎችን በመፍጠር ሳይመለስ በመቆየት የአድማጭን የማወቅ ጉጉት መጨመር ልብ ሰቀላ ይባላል።ልብ ሰቀላ አድማጩ ድራማውን በጉጉት፣በከፍተኛ ፍላጎት እንዲከታተለው የሚጠቅም ዋነኛ መሳሪያ ነው።በራዲዮ ተውኔት ልብ ሰቀላ የመሀዘን ድንጋይ ነው ማለት ይቻላል።ምክንያቱም አድማጩ ከዚህ ቀጥሎ ምን ይፈጠር ይሆን ብሎ ድራማውን እንዲከታተል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።የድራማው ግጭት እየተጋጋለ ወደ ላይ በሚወጣበት ጊዜ ልብ ሰቀላ ይፈጠራል።ይህ ደግሞ የአድማጩን ቀልብ ለመቆጣጠር እንደሚረዳ የታወቀ ነው።ልብ-ሰቀላ ዝምታን በመጠቀም፣ ሙዚቃን በማስገባት በተጨማሪም የተለያዩ ክስተቶችን በመጠቀም ሊፈጠር ይችላል።ቃለ ተውኔት ምልልሶችም ደግሞ ፈጣን ወይም ቀስ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ።ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው "በሚለው መጽሃፉ ስለ ልብ ሰቀላ ይህን አስቀምጧል።"በተውኔትም ሆነ በልቦለድ ድርሰት ውስጥ የ አንድን አጓጊ ድርጊት ፍጻሜ ለማውቅ የሚኖር ጉጉት ልብ ሰቀላ በመባል ይታወቃል።"(1993፣20)

2.6.6. ሴራ

ሴራ ማለት ምን ለምን ሆነ? ምን ለምን ተደረገ? ብሎ ለሚጠይቅ ምላሽ ያለው ምክንያታዊ እና ውጤት ያለው ለአንድ ተውኔት እጅግ አስፈላጊ የሆነ በዋናነትታሪኩ ላይ ቅመም/ጨው መጨመር ነው።ሴራ ታሪክ ሲደመር ግጭትና አህፅሮተተውኔት የምንለውን በዉስጡ ይዟል።ይህም ማለት ድርሰቱ ሲፃፍ የያዘው

ታሪክ ማለት ሊነገር ወይም ሊታወቅ የሚገባው ሀሳብ በዋናነት ሲኖር ይህም ፀሀፊው ቅደም ተከተል ብቻ ይዞ የፃፈው ምንም አይነት ምክንያትና ውጤት የሌለው ሀሳብ ማለት ነው።ሴራን ስንመለከት ደግም ታሪኩ ከመነሻው ጀምሮ እስከመጨረሻው ድረስ ለምን እና እንዴት ታሪኩ ውስጥ እንደገባ በምን ምክንያት እንደ ተፈጠረና በመጨረሻም ውጤቱ ምን እንደሆነ በምክንያት እና በውጤት ተሰናስሎ ሲቀርብ የምንመለከትበት/ለተደራሲያን የምናሳወቅበት ዘዴ ነው።ይህ አላባ በምክንያት እና በውጤት ተውቦ አሳማኝነትንም ጨምሮ የሚያዋዛልን ነው።የሻው ተሰማ "የተውኔት አፅናፍ መነፅር"በተሰኘው መፅሐፉ ላይ እንደዚህ ያብራራል"ሴራ ስንል የአንድን ጥበባዊ አካላት ከስር-ጫፍ የሚያደርስ የታሪክ የውስጥ ለውስጥ "ፈሮ" እንደሆነ ጠቁመናል ።ከስር-ጫፍ ማለታችን ሴራውን አሰባስቦ የሚያጣምራቸው የታሪክ ቁርጥራጮች ሊፈጠሩ እንደማይችሉ ለማመልከት ነው ።"(1998፣86)

ሴራ የታሪክ እና የግጭት ውጤት ነው።ሴራ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል የሚተርከው በምክንያት እና ውጤት ላይ ተመርኩዞ ነው። ሴራ የአንድ የጥበብ ስራ ማጣፈጫ ነው።ታሪክ እና ግጭት አንድ ላይ ተዳምረው የጥበብ ስራው እንዲቀጥል ያደርጉታል።የእነዚህም የታሪክና የግጭት ውጤት ሴራ ይባላል። ሳሙኤል ተስፋዬ እና ሌሎች ባዘጋጁት "የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር የጥናትና ምርምር ጆርናል"በሚለው መጽሃፍ ሴራን እንዲህ ይገልጻሉ።"ሴራ የአንድ ጥበባዊ ትረካን ከመሰረቱ እስከ ፍጻሜው የሚያያይዝ ወሳኝ አካል ነው።"(2009፣92)waldot Abbot ደግሞ Handbook of broad casting በሚለው መፅሀፉ ላይ ስለ ሴራ እንዲህ አስቀምጧል።"ሴራ በታሪኩ መጀመሪያ ላይ ግልፅ ሆኖ መታወቅ የለበትም።ግጭት ሊኖረው ይገባል።ጡዘቱ ያልተጠበቀ ፍፃሜ ሊኖረው ይገባል።አድማጩ ባልታሰበ አጨራረስ ነው ሊጨርስ ሚገባው።"[4] (1957፣196)

2.6.7.ግብአተ-ድምፅ

ግብአተ-ድምፅ በሬድዮ ድራማ ውስጥ መቼትን እና ድባብን በመግለጽ አድማጭ ድራማውን በስሜት እንዲያዳምጥ በአዘጋጁ አማካኝነት ተመርጠው ታሪኩን በተፈለገው እና በተገቢው መልኩ ድራማዊ ድርጊያውንም ሆነ መለእክቱን ለማስተላለፍ ያስችላሉ።ለምሳሌ የገፀ ባህሪውን መውጣት ና መግባት፣ በር መከፈት እና መዘጋት፣የወንዝ ዳር ቦታዎች...ወዘተ አድማጭ በምዕናቡ ምስልን እንዲስል ይረዳል።waldot Abbot Handbook of broad casting በሚለው መፅሀፉ ስለ ግብአተ ድምፅ ይህን ብሏል።"የራዲዮ ድራማ የተለያዩ ግብአተ-ድምፆችን ድባብን ለመፍጠር ይጠቀማል።"[5] (1957፣ 202)ስለ ግብአተ ድምጽ የሌሎች ምሁራንን ሃሳብ ስንመለከት ሳሙኤል ተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት "በሚለው መጸሃፉ ይህን

ያስቀምጣል።"ግብአተ ድምጽ የሚባለው ንግግርም ሙዚቃም ያልሆነ በርካታ ስሜቶች እና ሁነቶችን መግለጽ የሚችል ድምጽ ነው።"(2012፣161) በአጠቃላይ ግብአተ ድምጽ በአንድ የሬድዮ ስራ ውስጥ ስሜትን፣ጊዜ፣ቦታ እና ድራማዊ ድርጊያን ምስል ከመፍጠር አኳያ ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ነው።

2.6.8 ተራኪ

ተራኪ በድራማ ውስጥ ከሚሳሉ ገፀ ባህሪያት በገለልተኝነት የሚሳልና በድራማ ውስጥ መገለፅ ያለባቸውን ድርጊቶች የሚያብራራ ነው።በተጨማሪም በራዲዮ ተውኔት ውስጥ የተራኪ ሚና ተዋንያንን እና በራዲዮ ድራማ ውስጥ የተሳተፉ ባለሙያዎችን ማስተዋወቅ፣የድራማውን ክፍል ማሳወቅ...ወዘተ ነው። ተራኪ ከድራማው ታሪክ እና ድርጊት ተለይቶ በራሱ ምህዋር የሚሽከረከር የድራማው ደጋፊ ነው።waldot Abbot handbook of droad casting በሚለው መፅሀፉ እንደገለፀው"በራዲዮ ድራማ ውስጥ የተራኪ መግባት መቶ በመቶ ጠቃሚ ነው።ተራኪ አድማጩ ድራማው እየተሰራበት ያለውን መቼት /ጊዜናቦታ/በአህምሮ እንዲስል ያደርጋል።"[6] (1957፣198) ተራኪ ከዚህም በተጨማሪ ታሪኩንም በመተረክ ሊያስኬድልን እና አድማጭ ታሪኩን እንዲረዳ ያስችላል።

2.7. የራዲዮ ድራማ አላባዊያን

ራዲዮ ድራማ የራሱ የሆኑ አላባዊያኖች አሉት።እንደ ሌሎች የጥበብ ስራዎች ሁሉ የራዲዮ ድራማም ሙሉ ሆኖ ለአድማጭ እንዲደርስ አላባዊያንን ይጠቀማል።የራዲዮ ድራማ አላባዊያን ከተውኔትም በሆነ ከልቦለድ አላባዊያን የተለዩ ናቸው።ራዲዮ ድራማ በምስል የሚቀርብ ሚዲያ ባለመሆኑ አድማጭ በምህናቡ ምስልን እንዲከስት የሚያስችሉ አራት አላባዊያንን ይጠቀማል።Ruben Bermejo የተዘጋጀው The elemnts of radio በሚለው ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ የራዲዮ አላባዊያንን በ አራት ይከፍላቸዋል።የሰው ድምፅ፣ሙዚቃ፣ሳውንድ ኢፌክት፣ፀጥታ እንደ Ruben Bermejo አገላለፅ በዝርዝር ስንመለከት:-

2.7.1. የሰው ድምፅ

በራዲዮ ተዉኔት ዉስጥ ገጸ-ባህሪያትን የመናዉቃቸዉ፣ ቦታና ጊዜን የምንለየዉ በተዋንያኖች ድምጽ አማካኝነት ነዉ። አዘጋጁ ለራዲዮ ድራማ ተዋናይን ሲያዘጋጅ የፈለገዉን ድምጽ መፍጠር የሚቺሉ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ይኖችበታል። ምክኛቱም ተዋናዩ የተፈለገዉን ሁሉ በድምጻቸዉ ስለሆነ የሚያስተላልፉት የታዘዘዉን የመፍጠር አቅም(ችሎታ) ሊኖረዉ ይገባል። በአድማጭ ላይ ግርታን ላለመፍጠር። እንደ Ruben Bermejo አገላለፅ በዝርዝር ስንመለከት:- “ድምፅ በራዲዮ ላይ ትልቁን ሚና

ይጫወታል።በአድማጮች ላይ የተለያዩ ስሜትን መፍጠር ይችላል።ድምፃችንን ወይም ንግግራችንን በተገቢው መንገድ ካልተናገርን ለአድማጭ ግርታን ሊፈጥር ይችላል።ማለትም በዝግታ መናገር በንግግር ወቅት፣አለመጣደፍ፣አፍን ማንቀሳቀስ በንግግር ወቅት በተቻለ መጠን አፍን ማንቀሳቀስ ለጆሮ በሚመጥን መልኩ ማውጣት፣አለመሳቅ ድርሰቱ ላይ ከሌለ በስተቀር በንግግር ወቅት አለመሳቅ።"[7] (2017፤1)

2.7.2.ሙዚቃ

በራዲዮ ድራማ ውስጥ የመዚቃ ተለያዩ ስሜቶችን ለመደገፍ ወይም የተለያዩ ድባቦችን ለመፍጠር የገቡ ሙዚቃዎችን ማለታችን ነው።በድምፃዊ የተዘፈኑ ወይም በተለያዩ ሙዚቃ መሳሪያዎች የተቀነባበሩ ዜማዎችንም ያጠቃልላል።ሙዚቃ ለራዲዮ ድራማ ከሚያስፈልጉ አላባዎች አንዱ ነው። ራዲዮ ድራማ በሚዘጋጅበት ጊዜ ከራዲዮ ድራማው ጋር የሚሄዱ ድባብን የመግለፅ አቅም ያላቸው ሙዚቃዎች ላይ በደንብ ማሰብ ያስፈልጋል።እንደ Ruben Bermejo አገላለፅ ስንመለከት፡-
''ሙዚቃ በራዲዮ ላይ ጠቃሚ ነው።ሙዚቃ ለምናስተላልፈው መልዕክት የሚሆን ከባቢ አየርን ለመፍጠር ይረዳል።ሙዚቃ በዋናነት የምንጠቀመው መልዕክትን ለማስተላለፍ ሳይሆን አድማጭን እኛ ወደምንፈልገው ስሜት ለማምጣት ነው።በዚህም ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል።''[8] (2017፤4)

2.7.3.ዝምታ (ፀጥታ)

ዝምታ ፀሀፊው በቃለ ተውኔት መግለፅ የቸገረውን (አንዳንድ ጊዜ ቃላቶች የምንፈልገውን ምስል እና ድርጊት መስጠት ስለማይችሉ።)አድማጩ በዝምታው(በቃለተውኔት እና ቃለተውኔት መሀል እንዲሁም በቃለ ተውኔት እና ግብአተ ድምፅ መሀል፣በሙዚቃ እና በቃለ ተውኔት መሀል ወዘተ እንዳስፈላጊነቱ እየገባ)ውስጥ ድርጊቱን እና ምስሉን በምናቡ እንዲያገኘው የሚያግዝ እንዲሁም የቃለ ተውኔቱን ስሜት እና ድርጊት ይበልጥ ትርጉም ባለው መንገድ እንድንረዳ የሚያደርግ ነው።ያልተሰጡ ስሜቶችን የሚሰጥ ቴክኒክ ነው።ዝምታ ገፀባህርያቱ ያሉበትን ሁኔታ፣ቀጣይ ሊመጣ የሚችለውን ድርጊት በአጠቃላይ ድባቡን ሊነግረን ይችላል።እንደ Ruben Bermejo አገላለፅ ስንመለከት

"በራዲዮ ፕሮግራሞች ላይ ፀጥታ ብዙ ቦታ ባይሰጠውም ግን አስፈላጊ ነገር ነው አድማጭ ላይ ስሜትን የመፍጠር አቅም አለው።''[9] (2017፤7) ዝምታ በጥበብ ስራ ውስጥ የጉጉት ስሜትን ለመፍጠር የምንጠቀመው ነው።ይህ የድራማውን ከፍ ወይም የከረረ ገፅ የሚይዝ ክፍል ነው።ማለትም ማስፈራሪያ የሚሰነዘርበት፣ሙዚቃው እንደ መብረቅ የሚንጫረርበት ና ተራኪው የሞትን፣የጥፋትን፣ወይም በጎ ያልሆነን ድባብ እንዲሁም በጉጉት የሚጠበቁ የደስታ ስሜቶችን የሚተርክበት ነው።

2.7.4.ግብአተ ድምፅ

ግብአተ ድምፅ የምንለው በራዲዮ ድራማ ውስጥ የሚኖሩ ወይም የሚፈጠሩ በጆሮ የሚደመጡ ድራማውን ለመደገፍ የገቡ ምንም አይነት ድምፆች ናቸው።እነዚህ የሚገቡት ድምፆች የራዲዮ ድራማ በአይን መታየት ስለማይችል እየተፈጠረ ያለውን ነገር እንድንረዳ የሚያረጉን ድምፆች ናቸው።ለምሳሌ፡- የእቃ መሰበር፣የእግር ኮቴ፣የዝናብ፣የንፋስ፣የመብረቅ፣የበር መከፈትና መዘጋት፣የመኪና፣ የአውሮፕላን...ወዘተ ድምፆች በአስፈላጊው ሰዐት በተገቢው ስንጠቀማቸው ግብአተ ድምፅ(sound effect)ይባላል።እንደ Ruben Bermejo አገላለፅ ስንመለከት"ቃል ወይም ሙዚቃ ሳይሆን እራሱን የቻለ የድምፅ አይነት ነው።ይህንን ምንጠቀመው ከሙዚቃው ጋር በመሆን አድማጮች እየተካሄደ ያለውን ክንውን እንዲረዱ ለማድረግነው።[10] (2017፤9)

2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ ከምታጠናው ስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው እና በቤተ መፅሀፍት ውስጥ የሚገኙ ጥናታዊ ፅሁፎችን ቃኝታለች።እናም አጥኚዋ ከምታጠናው ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ጥናታዊ ፅሁፎችን አላገኘችም። በተዘዋዋሪ ከምትሰራው ጥናት ጋር የሚገናኙ ስራዎችን ተመልክታለች።

በተዘዋዋሪ ግንኙነት አለው ብላ የወሰደችው ጥናታዊ ፅሁፍ "ገፀ ሴት በለገዳዲ ራዲዮ ጣቢያ በተሰሩ ድራማዎች (1993-98ዓ.ም)"በበየነች አስፋው የተዘጋጀ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው።የበየነች ጥናታዊ ፅሁፍ እና ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያመሳስላቸው ሁለቱም በራዲዮ ድራማ ላይ መሰራታቸው ብቻ ነው።የበየነች ጥናት ከ1993-98ዓ.ም የተሰሩ ድራማዎችን ገፀ ሴት እንዴት ተገልፀዋ የሚለውን የሚገመግም ነው።ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግን ወፈ ቆመች የተሰኘውን የራዲዮ ከአላባዊያን አንፃር መመልከት ላይ ብቻ ያተኩራል።

አጥኚዋ በሁለተኛ የተመለከተችው ጥናታዊ ፅሁፍ በቆንሲል ተፈራ 1997 ዓ.ም የተሰራ "ግማሽ ጨረቃዎች"ተከታታይ የራዲዮ ድራማ ሂሳዊ ግምገማ በሚል ርዕስ ነበር የቀረበው።የቆንሲል ጥናት ሂሳዊ ግምገማ የሚሰጥ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማን አላባዊያን አጠቃቀም የሚመለከት ስለሆነ በዚህ ይለያያሉ።የቆንሲል ተፈራ ጥናት በምዕራፍ ሶስት የሴራ አወቃቀርን፣የቋንቋ አጠቃቀም፣ ጭብጥን፣የሙዚቃ አመራረጥ የሚሉ ርዕሶችን የሚተነትን ሲሆን ይህ ጥናት ግን ከአላባዊያን ማለትም የሰው ድምፅ፣ሙዚቃ፣ዝምታ፣ግብአተ ድምፅ የሚሉ ርዕሶችን ብቻ ያካተተ ነው።እነዚህ ሁለት ጥናቶች የሚያመሳስላቸው የሙዚቃ አጠቃቀምን(መግቢያ እና መሸጋገሪያ ሙዚቃን)፣የግብአተ ድምፅ አጠቃቀም፣ የሰው ድምፅ አጠቃቀም የሚሉ ርዕሶችን በማንሳት ይተነትናሉ።በዚህ ይመሳሰላሉ

ምዕራፍ ሦስት

3.የመረጃ ትንተና

3.1 የወፌ ቆመች ደራሲ እና አዘጋጅ ቀደምት ሰራዎች

መሃዛ ወርቁ በሀገራችን ካሉ ሴት ደራሲ እና አዘጋጅ መሀከል አንዷ ነች።መሃዛ ወርቁ በ1992ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትያትር ጥበባት የተመረቀች ሲሆን በመጀመሪያ በሙሉአለም ባህል ማህከል በትወና ዘርፍ በመሳተፍ ወደ ጥበቡ አለም መምጣት ችላለች።በመቀጠልም ፎዚያ የተሰኘ የቴሌቪዥን ድራማ ላይ አስተባባሪ(ማኔጀር)በመሆን አገልግላለች።ከዚህ ቀጥሎ **አቋራጩ** የተሰኘ የቴሌቪዥን ድራማን በ1994 ዓ.ም አዘጋጅታለች።ከእነዚህ ስራዎች በመቀጠል በ1995 ዓ.ም **የቅርብ ሩቅ** የተሰኘ በራሱዋ ተፅፎ በራስዋ ተዘጋጅቶ አድማጭ ጆሮ መድረስ የቻለ ባለ ሶስት ክፍል የራዲዮ ድራማን ሰርታለች።ከእነዚህ ሁሉ ስራዎች በፊት በመሃዛ ወርቁ ድርሰት እና ዝግጅት ለመጀመሪያ ጊዜ ለአድማጭ የደረሰው ስራዋ በኤፍ.ኤሜ 97.1 በዕለተ ቅዳሜ ይቀርብ የነበረ **ስርቅርቅታ** የተሰኘ አጭር የራዲዮ ድራማ ነው።ደራሲ እና አዘጋጅ መሃዛ ወርቁ ከራዲዮ እና ቴሌቭዠን ድራማዎች በተጨማሪ በርካታ የመድረክ ስራዎችን በመፃፍ እና በማዘጋጀት ለተመልካች ማቅረብ የቻለች የጥበብ ሰው ነች።ከሰራቻቸው የመድረክ ስራዎች መካከል ዝነኞቹ እና ከሰላምታ ጋር የተሰኙ የመድረክ ቴአትሮች ተጠቃሽ ናቸው። **ዝነኞቹ** የተሰኘው የመድረክ ስራ መሀዛ ወርቁ ለመጀመሪያ ጊዜ የፃፈችው የመድረክ ስራ ሲሆን የይህም ስራ ደራሲዋ ከተመረቀች ከአስር አመት በኃላ ማለትም በ2003 ዓ.ም ለእይታ የበቃ ነው። ይህ ቴአትር ለመጀመሪያ ጊዜ ለእይታ የቀረበው በአዲስ አበባ ባህል አዳራሽ ነው።በዚሁ አመት ሌላኛው ስራዋ **ከሰላምታ ጋር** የተሰኘው ሲሆን ይህ የመድረክ ስራ በመጀመሪያ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፈ ነበር።ደራሲዋ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ልትፅፍ የቻለችው በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት ቴአትር ቤቶች አሰራር ሊያንቀሳቅሷት ባለመቻላቸው በማንኛውም ቦታ ከቴአትር ቤት ውጪ መሰራት የሚችል ፅሁፍ ለመፃፍ እያሰበች ባለችበት ሰዐት በአሜሪካ የሚገኝ ስንዳንስ ኢኒስቲቲውት የተሰኘ የፊልም እና የመድረክ ስራዎች ላይ የሚሰራ ተቋምም በምስራቅ አፍሪካ ቴአትሮችን ለማወዳደር ጥሪ ያወጣሉ።መሀዛም በዚህ ውድድር ለመሳተፍ በመፈለግዋ ምክንያት ይህን ትያትር በእንግሊዝኛ ቋንቋ "**Desperate to fight**"በሚል ርዕስ ትፅፋለች። ይህ ስራ በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች መታየት የቻለ ስለነበር ለደራሲዋ ብዙ የስራ እድሎችን መክፈት ችሎ ነበር።"Desperate to fight"በምስራቅ አፍሪካ በኬንያ፣በሩዋንዳ፣ዩጋንዳ፣ቡሩንዲ ለእይታ በቅቷል።በስዊድ እና ኒዮርክ ታይቷል፣ በጀርመንኛ እና በሰርቢያ ቋንቋ ተተርጉሞ ለመድረክ በቅቷል።ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የፊልም እና የትያትር ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት በማስተማሪያነት ይጠቀሙታል።ከዚህ ሁሉ በኃላ ነው ደራሲዋ

በውስጧ ባለው ሃገሩዋን የመጥቀም ሀሳብ በመነሳሳት በድጋሚ በአማርኛ ቋንቋ "ከሰላምታ ጋር "በሚል ርዕስ ተርጉማ አፍሪካ ጃዝቪሌጅ ና ጃዛባ የሚባሉ ቦታዎች ላይ ለሁለት አመት መታየት ችሏል።ከነዚህ ስራዎች በተጨማሪ በቅርብ ጊዜ ድርሰት እና ዝግጅት በመሀዛ ወርቁ ሆኖ በ2012 ዓ.ም ለእይታ የበቃው "**ሼክስፔር ኢትዮጵያዊ ነው**።"የተሰኘው እና እንዲሁም "**ደርሶ መልስ**" ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ የቅርብ ጊዜ ስራዎቿ ምሳሌዎች ናቸው።

በመጨረሻም መሀዛ ወርቁ ከሰራቻቸው ስራዎች መካከል "**ወፌ ቆመች**"የራዲዮ ድራማ አንዱ መሆኑ ይታወቃል።ወፌ ቆመች በ2008 ዓ.ም ለአድማጭ የደረሰ ስራ ሲሆን ደራሲዋ ይህን የራዲዮ ድራማ ለመፃፍ ያነሳሳት በሰዐቱ በአዲስ አበባ የነበረው በከፍተኛ ሁኔታ በልማት ምክንያት ይነሱ(ይፍርሱ) የነበሩ ሰፈሮችን በተለይም ደራሲዋ በግሏ የምታውቀው ሪበከንቱ የተባለው ሰፈር በልማት በመነሳቱ ምክንያት ማህበረሰቡ መበታተን እና አጠቃላይ ያለውን ሁኔታ በተመለከተች ጊዜ የሰዎቹ መጨረሻ ምንድነው?ልማት እንደዚህ ነው?የከተማው የሚቀረው ታሪክ ምንድ ነው?የሚሉ ጥያቄዎች በውስጧ በመፈጠራቸው ይህን ሀሳብ ወደ ራዲዮ ድራማ ቀይራ በ2007/08 ለአድማጭ አድርሳለች።
መሀዛ ወርቁ በአሁን ሰዐት እየሞተ ያለውን የትያትር ጥበብ ለመታደግ በበጎ ፈቃደኝነት በጎ ፈቃደኞችን ሰብስባ ትያትርን የማዳን፣የመታደግ ስራ እየሰራች ትገኛለች።

በአጠቃላይ መሀዛ ወርቁ ከሃያ አመት በላይ በጥበብ ስራ ውስጥ የቆየች እና ለሀገራችን ብዙ ስራን ያበረከተች ወደፊትም ብዙ የጥበብ ስራዎችን በመስራት የሀገራችንን የጥበብ ኢንዱስትሪ ለማሳደግ ተፅህኖ ፈጣሪ ተብለው ከሚጠበቁ የጥበብ ሰዎች ዋነኛዋ ነች።

3.2የወፌ ቆመች ራዲዮ ድራማ ባለሙያዎች

ደራሲና አዘጋጅ፡ መሀዛ ወርቁ።

ተራኪ፡ተፈራ አለሙ።

ተዋንያን፡አለማየሁ ታደሰ፣ሙሉአለም ታደሰ፣አቤል ሰለሞን፣ቃልኪዳን አበራ፣ማርታ ሀ/እየሱስ፣ፍቃዱ ከበደ መሰረት ህይወት፣አቤል ሀጎስ፣ዘሪሁን ብርሀኑ፣ባዩሽ አለማየሁ፣ተስፋዬ ይማም፣አይቼሽ እሸቱ፣ ቅድስት ገ/ስላሴ፣ትነበብ ተረፈ፣ቤተልሄም ታየ፣ማርታ ሀይለየሱስ እና ሌሎች ተጋባዥ ተዋንያን ተሳትፈውበታል።

ድምፅ ቀረፃ፡አብደላ መሀመድ።

3.3የወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ታሪክ

‹ወፌ ቆመች› አስቂኝ ይዘት ያለው የቤተሰብ ታሪክ ድራማ ነው፡፡ አቶ አማረ ባለቤቱን ለውጪ ትምህርት ጀርመን ሀገር ልኮ ባይሳካለትም እናትም አባትም ሆኖ እያሳደገ ያለ አባዎራ ነው፡፡የአቶ አማረ መኖሪያ ለልማቱ ከተነሱት ቤቶች አንዱ ሆኗል፣ በቀነ ጎዶሎ ከስራውም ተሰናብቷል፡፡አቶ አማረ አባቡ፣እድላዊት እና ሰላም የተባሉ ልጆች አሉት፡፡የ‹ወፌ ቆመች›ድራማ በ3 ምዕራፎች ይከፈላል፡፡ ምዕራፍ ፡ /ከክፍል ፡ እስከ 12/፤ ለልማት ተነሺ በሆነ ‹ሞጃ ሰፈር› የተባለ ምናባዊ ሰፈር ያተኩራል፡፡ አባወራው አቶ አማረ በፍጥነት በመነሳት ላይ ባለው ሰፈሩ ምክንያት ቤቱን እና ቤተሰቡን ለማደላደል ይጣጣራል፡፡ ስራ የለውም፣ሚስቱ አጠገቡ የለችም፣ልጆቹን ጨምሮ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ግራ ተጋብተዋል፡፡ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ ቤት ለመገንባት ይፍጨረጨራል፡፡ የቤት እቃዎቹን ይሰበስባል፣ያሳስራል፣ኮተት ያለውን ይጥላል፣ከጎረቤቶቹ ጋር ይጣላል፣ይሰነባበታል፡፡ ምዕራፍ 2 /ከክፍል 13 እስከ 26/ አቶ አማረ አዲስ መኖሪያ ከከተማው ወጣ ባለ ቦታ በፍጥነት ቤት ሰርቷል ፡፡ እንደ ቤተሰብ ከተዋሀዳቸው የደሀ ሰፈር ‹ሞጃ ሰፈር› ጎረቤቶቹ ተለይቶ ከባለፀጋ ጎረቤቶቹ ጋር ለመላመድ ይሞክራል፡፡ በቤተሰቡ እና በጎረቤቶቹ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት የሰማይ እና የምድር ይሆንበታል፣መስራት፣መነጋገር፣ መግባባት ይቸግረዋል፡፡ የበታችነት ፣ብቸኝነት ሲሰማው ቤተሰቡን ጠቅልሎ አዲሱን ቤቱን አከራይቶ ሰፈሩን ይለቃል፡፡ ምዕራፍ 3 /ከክፍል 27 አስከ 36/ አቶ አማረ የግል ቤቱን አከራይቶ ኮንደሚኒየም ተከራይቶ መሀል ከተማ ገብቷል፡፡ የኮንደሚኒየም ኮሚቴ ጉዳይ ስራ አስኪያጅም ተደርጎ ተቀጥሯል፡፡ ለአቶ አማረ ቤተሰብ የኮንደሚኒየም ህይወት ራሱን የቻለ ሌላ አለም ሆኖባቸዋል፡፡ ይዋደዱበታል፣የገረሙበታል፣የሰሩበታል፣ይተሳሰሩበታል፡፡

ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ በመሀዛ ወርቁ ተዘጋጅቶ በሸገር **ኤፍ.ኤም 102.1** በእውነተኛ ሁነቶች ላይ ተመስርቶ በየክፍሉ የተለያዩ ሀሳቦችን ይዞ በሳምንት አንድ ጊዜ የሚቀርብ አስቂኝ ይዘት ያለው የቤተሰብ ድራማ ነው። በዚህ ድራማ ውስጥ አንጋፋ ተዋንያን የተሳተፉበት ሲሆን እነሱም ዋና ገፀ ባህሪያትን የሚጫወቱት አለማየሁ ታደሰ፣ሙሉአለም ታደሰ፣ቃልኪዳን አበራ፣አቤል ሰለሞን ናቸው።ዋናው ታሪክ ሞጃ በተባለ ሰፈር ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች ቦታው ለልማት በመፈለጉ ምክንያት ከቤታቸው መፈናቀላቸውን ምክንያት አድርጎ በውስጡ ግን የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት የሚዳስስ ነው።ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ በሦስት ምዕራፎች ይከፈላል።በአጠቃላይ አርባ ክፍሎች ያሉት ሲሆን አጥኚዋ ከእነዚህ ክፍሎች ለማሳያነት ይሆኑ ዘንድ ከየምህራፉ አምስት አምስት ክፍሎችን በመውሰድ ከራዲዮ አላባዊያን አንፃር ትተነትናለች።አጥኚዋ ከየምህራፉ የተመረጡ ክፍሎችን በመውሰድ ጥናቱን የምታካሂድ ሲሆን እነዚህም

የተመረጡ ክፍሎች ለምሳሌነት የምታቀርባቸውን ነጥቦችን የያዙ ስለሆኑ እነዚህን ክፍሎች ለምሳሌነት ልትመርጥ ችላለች።

3.4 . "ወፌ ቆመች"የራዲዮ ድራማ ከአላባዊያን አንጻር

3.4.1."ወፌ ቆመች"የራዲዮ ድራማ ከሙዚቃ አጠቃቀም አንፃር

ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ አዘጋጅ በርካታ ሙዚቃዎችን ተጠቅማለች።የመግቢያ እና የመሸጋገሪያ ሙዚቃዎችን ስንመለከት"የመግቢያ ሙዚቃ"በሁሉም ምህራፎች ላይ አንድ አይነት የመግቢያ ሙዚቃ ብትጠቀምም "የመሸጋገሪያ ሙዚቃ"ደግሞ በየምዕራፉ የተለያዩ (ለሶስቱም ምዕራፎች) የተለያየ የመሸጋገሪያ ሙዚቃ ነው የተጠቀመችው።ይህ ደግሞ የራዲዮ ድራማው ብዙ ክፍሎች ስላሉት ድግግሞሽ እንዳይኖረው እና በአድማጭ ላይ መሰላቸትን እንዳይፈጥር በየምህራፉ አዲስ ነገርን ለመፍጠር ተሞክሯል።ይህ እንደ ጠንካራ ጎን ልንመለከተው እንችላለን።በሌላ በኩል የመግቢያ እና የመሸጋገሪያ ሙዚቃ መመሳሰል የለበትም።ድራማው ሲጀምር እና ድራማው ከትዕይንት ወደ ትዕይንት ሲሸጋገር የተለያዩ(ተመሳሳይነት የሌላቸው) ሙዚቃዎችን ነው መጠቀም ያለብን።አድማጭ ድራማው ሲጀምር እና ሲያልቅ እንዲሁም ከትዕይንት ወደ ትዕይንት መሸጋገሩን ያለ ግርታ መለየት መቻል አለበት።
ወፌ ቆመች የመግቢያ እና የመሸጋገሪያ ሙዚቃ አጠቃቀም እጅግ ጥሩ እና በመግቢያ እና በመሸጋገሪያ ሙዚቃ መሀል ያለው ልዩነት ግርታን የማይፈጥር ነው።እንዲሁም የራዲዮ ድራማው አስቂኝ በመሆኑ የተጠቀሙት የሙዚቃ ምርጫ ከስራው ጋር የሚሄድ ነው።

3.4.1.1.ሙዚቃ ከገፀ-ባህሪ አንፃር

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የሙዚቃ አጠቃቀም ገፀ ባህሪያትን እንዴት ገልፀዋል? ወይም እንዴት የገፀ ባህሪትን ስሜት ደግፏል?የሚለውን ስንመለከት፡-

በክፍል ሰላሳ ሰባት፡በደቂቃ 26፡42 ላይ የገፀ ባህሪውን የሀዘን፣የፍቅር ፣የመጨነቅ እና በአጠቃላይ የገፀ ባህሪውን ውስጣዊ ስሜት ለማጉላት የተጠቀሙት የዳዊት ፅጌን "እንዴት አድርጌ"የተሰኘ ሙዚቃ በተገለጸው የድራማ ክፍል ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር የገፀ ባህሪውን ስሜት በአድማጮቹ ዘንድ በማጋባት ፣ አድማጮች በሚገባ ስሜቱን እንዲረዱት ማድረግ የቻለ ነበር።

በክፍል ሦስት፡-13፡06ሰላም በቴዲ መምጣት መደሰቷን ለማሳየት ከጀርባ ከገባው "የሚካኤል በላይነህ"ሙዚቃ ጋር አብራ መዝፈኗ አድማጭ ደስታዋን እንዲረዳ አድርጓል።

በክፍል ሃያ ስምንት፡-12:06 የአስቴር አወቀ ሙዚቃ የአባቡ እና የማህሌት የፍቅር ንግግርን ለመደገፍ የገባው ዘፈን በሚገባ ያሉበትን የፍቅር ስሜት ለአድማጭ ማጋራት ችሏል።
19:55 "ትደገም ቅዳሜ"የሚል ሙዚቃን ሰላም እና ቤቢ አብረው ከፍ ባለ ድምፅ ሲያዜሙ ውሎዋቸው ደስ የሚል እንደነበረ አድማጭ ከቃለ ተውኔት ቀድሞ እንዲረዳ አድርጓል።

3.4.1.2.ሙዚቃ ከታሪክ አንፃር

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ ያሉ ሙዚቃዎች ታሪኩን ከመግለፅ አንፃር ስንመለከታቸው፡-ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ አስቂኝ ይዘት ያለው እንደመሆኑ በመግቢያ እና በመሸጋገሪያ ላይ ያሉት ሙዚቃዎች ፈጠን ያሉ እና የተውኔቱን የታሪክ ጉዞት መፍጠን የሚያነሉ ሙዚቃዎች በመሆናቸው ታሪኩን ደግፈውታል ለማለት የሚያስችል ነው።

3.4.1.3ሙዚቃ ከመቼት አንፃር

የወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ የሙዚቃ አጠቃቀም የድራማውን ቦታ እና ጊዜ፣ማህበራዊ ሁኔታ ገልጿል?የሚለውን ስንመለከት በሚፈለገው እና ተገቢ በሆኑ ቦታዎች ላይ የገቡ ሙዚቃዎች አድማጩ ቦታው የት፣መቼ እንደሆነ ፣ምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳለ እና የተፈለገውን ድባብ አድማጩ እንዲረዳ አግዘዋል።ለምሳሌ፡-
በክፍል አንድ፣በደቂቃ 21:57 ላይ የካፌ ወይም የሆቴል ቤት ድባብን ለመፍጠር የተጠቀሙት የእዮብ መኮንን "ከአንቺ በላይ"የሚለው ለስለስያለ ሙዚቃ የተከፈተበት ድምፅ መጠኑ ቀነስ ተደርጎ ከሰዎች የጫጫታ ግብዐተ ድምፅ ጋር ተዳምሮ ገፀ ባህሪው በሆቴል ወይም በካፌ ውስጥ እንዳለ ለመረዳት ችለናል ይህም የተፈለገውን የሆቴል ቤት ድባብ መፍጠር ችሏል።ወፌ ቆመች **በክፍል አስራ ሁለት** በደቂቃ **00:59** ላይ የልደት ፕሮግራም ላይ የተከፈተው የልደት ዘፈንም ጥሩ የሙዚቃ አጠቃቀም ምሳሌ ነው።
በክፍል አስራ አምስት፡-9:08 ላይ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ መዝሙር የሚሰማ ሲሆን አማረ ቤተክርስቲያን እንደሆነ ያሳየናል።
ወፌ ቆመች **በክፍል ሰላሳ ሰባት** ደቂቃ **14:07** ላይ የጭፈራ ቤት ድባብን ለመፍጠር ከተዋናዮቹ ምልልስ ጀርባ የተከፈተው የእንግሊዘኛ ሙዚቃ ጥሩ የጭፈራ ቤት ድባብን ፈጥሯል።

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ የሙዚቃ አጠቃቀም ላይ ያለ አግባብ የገቡ ሙዚቃዎችን እንደምሳሌነት የተጠቀሱ ቦታዎችን ስንመለከት 33:59 ከገፀባህሪያት ምልልስ ጀርባ የገባው ሙዚቃ ገፀባህሪያቱ ከሚያነሱት ሀሳብ ወይም ገፀ ባህሪያቱ በቤት ውስጥ በቴፕ የከፈቱት ድምፅም አይደለም።15:59 ከቃለ

ተውኔቱ ጀርባ በማጀቢያነት የገባው "የማሚላ ሉቃስ"ሙዚቃ ሀሳቡን የማይደግፍ የታሪኩን ድባብ የማይገልፅ ነው።

3.4.2 ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ከግብአተ ድምፅ (sound effect) አንፃር

ግብአተ ድምፅ በራዲዮ ድራማ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ነው።ግብአተ ድምፅ በራዲዮ ድራማ ላይ ሕይወት የመዝራት አቅም አለው።በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የግብአተ ድምፅ አጠቃቀም ስንመለከት ጥሩ የሚባል ነው።የተጠቀሚቸው ግብአተ ድምፆች ሰአታቸውን ጠብቀው በተገቢው ሰዐት በመግባታቸው የተፈለገውን ስሜት መፍጠር ችለዋል።ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ምሳሌዎችን ከየምዕራፉ ሁለት ከፍል ወስደን እንመለከታለን።

3.4.2.1ግብአተ ድምፅ ከገፀ ባህሪ አንፃር

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የግብአተ ድምፅ አጠቃቀም ገፀ ባህሪያትን ከመግለፅ፣ስሜታቸውን ከመደገፍ እና ያሉበትን ቦታ ከማሳወቅ አንፃር እንዴት ይቃኛል?የሚለውን ስንመለከት፡-

በክፍል አንድ 28:50 ፍሬ ገነት ቡና ልታፈላ መሆኑን በቃለ ተውኔት ትነግረን እና ማፍላቷን ለማሳወቅ የገባ የሙቀጫ(የቡና መወቀጥ)ድምፅ በቃለ ተውኔት የነገረችንን ድርጊት በግብአተ ድምፅ ደግፈዋታል።

በክፍል ሦስት፡-26:58 አማረ መንገድ ላይ እየተራመደ መሆኑን ለማሳወቅ የፈጠነ የእግር ኮቴ መጠቀማቸው ገፀ ባህሪው የንዴት ስሜት ውስጥ እንዳለ ለማወቅ እረድቷል።

በክፍል አስራ ሁለት፡29:54 የቤት ስልክ ጥሪ ይሰማል ይህም ገፀ ባህሪያቶቹ ከእጅ ስልክ በተጨማሪ የቤት ስልክ ተጠቃሚ መሆናቸውን እንድናውቅ ረድቶናል።ብተጨማሪም የቤት ስልክ ጥሪው ገጸ ባህሪዎቹ በቤት ውስጥ መሆናቸውን ያመላክታል።

በክፍል አስራ ሶስት፡16:46 ፍሬ ገነት ጎረቤት ፍለጋ ሄዳ የበር ደውል ስትጫን የገባው በትክክልም የጥሪ ደውልን ገልጿል።በር ማንኳኳቷን ገልጿል።

በክፍል ሀያ ስድስት፡9:07 ቤቢ ንዴቱን ለመግለፅ የአማረ ቤት ላይ ዲንጋይ ሲወረውር የገባው ግብአተ ድምፅ የቤቢን የንዴት ስሜት በአድማጩ ዘንድ እንዲጋባ በማድረግ ደግፏል።

በክፍል ሰላሳ ሰባት፡1:08 አማረ ልጆቹን ለስብሰባ ሲጠራ ልጆቹ ስራ ይዘው እንደነበረ ለማሳወቅ የማንኪያ፣የሲኒ መጋጨት እና የእቃዎች መንኮሻኮሽ ይሰማ ነበር።ይህም የነበረውን የገፀ ባህሪያቶቹ የስራ ድባብ ፈጥሯል።29:05 ሰላም በቴዲ ቀንታ ናኒን በጥፊ ስትመታት የሰላምን የንዴት፣የቅናት ስሜት ደግፏል።

በክፍል አስራ አምስት፡-18:16 ፍሬ ገነት እና የአማረ እናት በሚወያዩበት ጊዜፍሬገነት በአማረ እናት መናደዷን ለማሳየት የመክተፊያውን ፍጥነት ትጨምረዋለች እንዲሁም በሀይል የበር መከፈት እና መዘጋት ይሰማል ይህም ፍሬገነት የንዴት ስሜት ውስጥ እንዳለች ያሳያል።

3.4.2.2.ግብአተ ድምፅ ከመቼት አንፃር

ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ በግብአትነት የገቡ ድምፆች የድራማውን ጊዜውን፣ቦታውን፣ማህበራዊ ሁኔታውን እንዴት ገልፀውልናል የሚለውን ስንመለከት፡-የወፌ ቆመች ራዲዮ ድራማ ግብአተ ድምፅ ጥሩ የሚባል ነው።መቼትን ከመግለፅ አንፃር ምሳሌ ስንመለከት

በክፍል አንድ፡27:13 ሰላም እና አባቡ ወደ ቤት ለመግባት በር ላይ ሲመካከሩ የገባው የነፍሳት ድምፅ በሚገባ ምሽት መሆኑን ጊዜውን ገልጿል።28:41 የቆርቆሮ በር ሲከፈት የገባው ድምጽ ከርቀት በመሆኑ የውጭ በር መሆኑን እንድንረዳ እና 29:04 ዋናው የሳሎን በር ሲከፈት ከቅርበት ያለው ድምፅ ገፀ ባህሪዎቹ ወደ ቤት መግባታቸውን ነግሮናል።

በክፍል አስራ አምስት፡-0:56 ላይ ጊዜው ጠዋት መሆኑን ለመግለፅ የወፎች ጫጫታ የሰማል።

በክፍል ሃያ ዘጠኝ፡-02:27 ፍሬገነት እና መልኬ የተባሉ ገፀ ባህሪያት በሚነጋገሩበት ወቅት የልጆች ጫጫታና የንፋስ ድምፅ መግባቱ ገፀ ባህሪያቱ ከቤት ውጪ መሆናቸውን ገልፆልናል።

በክፍል ሃያ ስድስት፡16:37 አማረ በጎዳና ላይ እየተራመደ ፣ የሚያልፉ የመኪናዎች ድምፅ እና የትልቅ መኪና ጡሩምባ (ክላክስ) ገፀ ባህሪው መንገድ ላይ መሆኑን ወይንም ያለበትን አካባቢ እንድንረዳ አርጎናል።23:06 የወፍ፣የአሞራ ድምፅ፣የሚንኳኳ ቆርቆሮ ድምፅ ጎላ ብሎ መሰማቱ ቦታው ጭር ያለ መሆኑን ገልጿል።

3.4.2.3ግብአተ ድምፅ ከታሪክ አንፃር

የወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ታሪክ ከንውኑ አንድ በልማት ምክንያት እየፈረሰ ባለ ሞጃ በተባለ ምናባዊ ሰፈር ላይ ነው።እናም በዚህ ድራማ ውስጥ ያሉ ግብአተ ድምፆች ታሪኩን ደግፈውታል ወይም ገልፀውታል የሚለውን ስንመለከት፡-አዘጋጇ የተጠቀመችው ግብአተ ድምፅ በሚገባ ታሪኩን እንድንረዳ አድርጎናል።ለምሳሌ፡-ታሪኩ የሚጀምረው ሰፈሩ በመፍረስ ላይ እያለ ነው ይህንም ለመደገፍ (ታሪኩን ለማስኬድ)አድማጭ ታሪኩን እንዲረዳ

በክፍል አንድ 1:09 በመፍረስ ላይ ያለን ሰፈር ድባብ ለመፍጠር የሚቀጠቀጥ ቆርቆሮ፣የሚወድቅ ዲንጋይ ድምፅ ተጠቅመዋል።

በክፍል አስራ ሁለት፡ታሪኩ የሚጀምረው የሰላም ልደት እየተከበረ ነው።ይህን ታሪክ ለመደገፍ በ11:43 ላይ የነበረው ግርግር ብርጭቆ ከብርጭቆ ጋር ሲጋጭ ፣ከሰዎች ጫጫታ ጋር ተደምሮ የልደቱን ድባብ ፈጥሯል ይህም ታሪኩን ደግፏል ለማለት ያስችላል ።

በክፍል ሃያ ሰባት፡ታሪኩ የሚጀምረው አማረ እና ቤተሰቦቹ ቤት ሲቀይሩ ነው።አድማጭ ቤት መቀየራቸውን እንዲረዳ በታሪኩ ግርታ እንዳይፈጠር እና ግልፅ እንዲሆን ከቃለ ተውኔት በበለጠ ግብአተ ድምፅን ተጠቅመው ታሪኩን ለመንናገር ተሞክሯል።3:00 አባቡ እና አማረ ቁምሳጥን ተሸክመው ሲገቡ፣ እቃዎች ሲያጓጉዙ የፌስታል መንኮሻኮሽ፣እንደ ቁም ሳጥን ያሉ ከበባድ እቃዎች ሲጋጩ የሚገልፁ ግብአተ ድምፆች ከሰው ድምፅ ጋር ተዳምረው ከቃለ ተውኔቱ ቀድመው ታሪኩን ሊያስረዱን ችለዋል።

24:59 የሜላት አጎት አባቡን በመኪና ሲገጨው ገፀ ባህሪያት በቃል ምልልስ ከመግለፃቸው በፊት የገባው ግብአተ ድምፅ ..የአባቡን መገጨት ቀድሞ እንድናውቅ ረድቶናል።ታሪኩን ነግሮናል።

የወፌ ቆመች የግብአተ ድምፅ አጠቃቀም ታሪክን፣መቼትን፣ገፀ ባህሪን ከመግለፅ፣ከመደገፍ አንፃር ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው የተፈለገውን ድባብ መፍጠር የቻለ ቢሆንም አንዳንድ ጉድለቶችም አሉ።

በክፍል አስራ ስድስት፡-30:52 ላይ የሚሰማ የማታን ድባብ ለመፍጠር የተጠቀሙት የውሻ እና የወፎች ድምፅ ሲሆን የተሰማው የአህዋፍ ዝርያ ከሆነው አንዱ ቁራ(አሞራ) ነው።አሞራ ደግሞ ማታ ማታ የሚጮህ አይደለም።

በክፍል ሃያ ስድስት 9:07 ላይ በቤቱ ላይ ድንጋይ እየተወረወረ መሆኑን ለማሳወቅ የተጠቀሙት ግብአተ ድምፅ ድንጋይ ከቆርቆር ጋር ሲጋጭ የሚፈጥረውን ድምፅ መፍጠር ባለመቻሉ እንደ ክፍተት

ተመልክቼዋለው።30:43 የሞባይል ስልክ መጥራቱን ለማሳወቅ ግብአተ ድምፅ ቢጠቀሙም ድምፁ ከፍ ያለ በመሆኑ በቴፕ የተከፈተ እንጂ የሞባይል ጥሪ መምሰል አልቻለም።

በክፍል ሃያ ሰባት፡3:00 አባቡ ና አማረ ቁምሳጥን ለማስቀመጥ ሲሞክሩ ያስቀመጡበት እና የገባው ግብአተ ድምፅ (ቃለ ተውኔቱን እና ግብአተ ድምፁ)ባለመጠባበቁ መግባት ባለበት ሰዐት ባለመግባቱ የተፈለገውን ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን አዛብቶታል።8:21 ቁምሳጥን ሲወድቅ እንጨት ሳይሆን ብረት የወደቀ ነበር የሚመስለው የእንጨት ድምፅን አልፈጠረም።

በክፍል ሰላሳ ሰባት፡29:05 ሰላም በቴዲ ተናዳ ናኒን በጥፊ ስትመታት የጥፊ ድምፅን ለማምጣት የተጠቀሙት ግብአተ ድምፅ የተፈለገውን ስሜት(የምት ድምጽን) አልፈጠረም።

በአጠቃላይ በእነዚህ በተመለከትናቸው ክፍሎች ውስጥ አዘጋጇ የተጠቀመቻቸው የግብአተ ድምፆች በሚገባ ቦታ እና ሰዐት ተስተካክለው በመግባታቸው ድራማውን በይበልጥ እንድንረዳው፣እንድንወደው፣ የራዲዮ ድራማውን በአይን እንደሚታየው ፊልም ሳንሰላች እንድንከታተል ረድተውናል።ይህም የወፈቆመች ግብአተ ድምፅ አጠቃቀም ጠንካራ ነው እንድንል ያስችለናል።

3.4.3 ወፈ ቆመች ከሰው ድምፅ አንፃር

በራዲዮ ተውኔት ውስጥ የሰው ድምፅ ዋናውን ሚና ይወስዳል።የተዋናዮችን ባህሪ፣ጊዜ እና ቦታን፣ሁሉን እየተካሄደ ያለን ነገር የምንረዳው በተዋናዮች ድምፅ ነው።እናም በዚህ ርዕስ በወፈቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ አዘጋጇ የተጠቀመቻቸው ተዋናዮች ድምፃቸውን በተገቢው እና በተፈለገው፣በአግባቡ ተጠቅመው የተፈለገውን ስሜት እና ድባብ ሰጥተዋል ወይም የገፀ ባህሪ እና የቦታና ጊዜ ትውውቅን በአግባቡ አስተላልፈዋል ወይ የሚለውን እንመለከታለን።

ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማ ተዋንያን የድምፅ አጠቃቀም ገፀ ባህሪያትን ገልጿል ወይ የሚለውን ስንመለከት።አዎ!በደንብ ከገፀ ባህሪያት ጋር አስተዋውቆናል። የሰው ድምፅ አጠቃቀም የወፈ ቆመች ዋነኛ ጠንካራ ጎኑ ነው።ተዋንያን በሚያደርጉት የቃል ምልልስ እያንዳንዳቸው ገፀ ባህሪያት ምን አይነት ፀባይ እንዳላቸው መረዳት ችለናል።ከቃል ምልልስ እንደተረዳነው የገፀ ባህሪትን አሳሳል ስንመለከት

3.4.3.1የሰው ድምፅ ከገፀባህሪ አንፃር

የወፌ ቆመች ገፀ ባህሪያትን አሳሳል ስንመለከት ደራሲዋ ታሪኩን የሚያራምዱላት በርካታ ገፀ ባህሪያትን ተጠቅማ እናገኛለን።ነገር ግን በዋናነት በዚህ ድራማ ውስጥ ትልቅ ሚና ይዘው የምናገኛቸው አማረ ፣ ፍሬገነት፣ሰላምና አባቡ ናቸው።እነዚህን ገፀ ባህሪያት ያላቸውን ባህሪ ስንመለከት

አማረ ባለትዳር፣የሶስት ልጆች አባት፣መካከለኛ ገቢ ያለው፣ የኮንደሚኒየም ነዋሪዎች ጉዳይ አሰፈፃሚ(..)ነው።አማረ፡-ተጫዋች(ክፍል አንድ ላይ **07:18** ፍሬገነትን ድምፁን ቀይሮ ሲያጫውታት ተጫዋች መሆኑን መመልከት እንችላለን።)ቀልደኛ(በክፍል አንድ ላይ **01:26** የቤት ፍራሽ ዲንጋይ ሰው ላይ እየወደቀ እሱ ግን ይስቅ ነበር።ኮሰታራ ሰው ቢሆን ይህን አያደርግም በዚህ የአማረን ቀልደኛነት በጥቂቱ መረዳት እንችላለን።ባለ ትዳር፣የሶስት ልጆች አባት(በክፍል አስራ ሶስት በደቂቃ **20:20** ላይ ከወ/ሮ ዘውዴ ጋር በምታደርገው ምልልስ አማረ የሦስት ልጆች አባት መሆኑን ገልፃለች።

ፍሬገነት፡-ያላገባች(በክፍል ሃያ ስድስት **07:24** ላይ ጥጋቡን እንደምታገባው ትናገራለች። ተጫዋች(በአብዛኛው ቃለ ምልልስ ላይ ሳቂታ ና ተጫዋች መሆኑዋን ማየት ይቻላል።ነጭናጫ(በክፍል አስራ ሁለት **08:16** ላይ ብር ጠፍቷት ብርጭቆ ስትጠየቅ መነጫነጯን ማሳያ ምሳሌ ይሆናል።

ሰላም፡-ቀበጥ፣የአስራ ሰባት አመት ልጅ:-ሰላም ቀበጥ መሆኑዋን ከሁሉም ገፀ ባህሪያት ጋር የምታደርገውን የቃል ምልልስ የድምፅ አወጣጧ ይገልፃል።የአስራሰባት ዓመት ልጅ መሆኑዋ ደግሞ ብዙ ቦታ ቢገለፅም እንደ ምሳሌነት፡-ፍሬገነት በክፍል አስራ ሶስት **20:28** ላይ ለወ/ሮ ዘውዴ ቤተሰቧን ስታስተዋውቅ ሰላም አስራ ሰባት አመቷ መሆኑን ትናገራለች።በክፍል አስራ አራት ላይ ቤቢ "አጠር ያለችውን ልጅ ጥራልኝ"ሲል ሰላም አጠር ያለ ቁመት እንዳላት ልናውቅ ችለናል።

አባቡ፡-ከሰው ተግባቢ፣የአስራዘጠኝ አመት ልጅ;-አባቡ ከሰው ተግባቢ መሆኑን በክፍል አስራሁለት **08:18** ላይ ፍሬ ገነት ብሯን ማስመለስ የሚችለው ተግባቢ በመሆኑ አባቡ ብቻ መሆኑን ትናገራለች።የአስራዘጠኝ አመት ልጅ መሆኑን በክፍል አስራ ሶስት **2:26** ላይ አባቡ አስራዘጠኝ አመቱ መሆኑን ፍሬገነት ለወ/ሮ ዘውዴ ስታስረዳ ማወቅ ችለናል።በአጠቃላይ በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ላይ ገፀ ባህሪያትን በማስተዋወቅ ደረጃ ገፀ ባህሪያቶቹ በሚገባ እንድንረዳቸው ተደርገው ተስለዋል።ተዋንያኑም የተሰጣቸውን ገፀ ባህሪ በሚገባ በአግባቡ በመጫወታቸው በቀላሉ የገፀባህሪያቱን ባህሪ ተረድተናል።

3.4.3.2የሰው ድምፅ ከመቼት አንፃር

ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የገፀ ባህሪያት የቃል ምልልስ ምን ያህል መቼቱን እንድናውቅ ረድቶናል የሚለውን ስንመለከት፡-ገፀ ባህሪያት ባላቸው የቃል ምልልስ የት?ምን ሰዓት ላይ ምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ለመረዳት ችለናል።ለምሳሌ፡-

በክፍል አንድ፡-የሞጃ ሰፈር ሲፈርስ አማረ 1፡26 ደቂቃ ላይ "ኧረ ይህ ፍራሽ ድንጋይ አናትህን ብሎህ ነበር"በሚለው ቃለ ተውኔቱ እየፈረሰ ያለው ሰፈር መሀል እንዳለ ያስረዳል።13:42 አባቡ እና ሰላም በሚያደርጉት የስልክ ምልልስ ሰላም ከጓደኞቿ ጋር ካፌ መሆኑዋን አባቡም ከጓደኞቹ ጋር ኳስ ለማየት DSTV ቤት መሆናቸውን ይገልፃሉ።

በክፍል ሦስት፡-13:36 አባቡ የተባለው ገፀ ባህሪ "ወንድሜ ሸቤ ገባህ"በሚለው ቃለ ተውኔት እና""ከፈቺ እና ምግቡን ቅመሺው"በሚል ቃለ ተውኔት ቦታው እስር ቤት መሆኑን ለመረዳት ችለናል።

በክፍል አስራ ሁለት፡-12:36 የብዙ ሰዎች ንግግር (ጫጫታ)በቦታው ብዙ ሰዎች እንዳሉ እና "ይቀዳልን እንጂ" በሚል ቃለ ተውኔታቸው(ጫጫታ) ቦታው ብዙ ሰው ያለበት ፕሮግራም መሆኑን መረዳት እንችላለን።

በክፍል አስራ ሶስት፡-2:30 ፍሬ ገነት ለወ/ሮ ዘውዴ ቤተሰቧን ስታስተዋውቅ ሀረግ ለትምህርት ወደ ጀርመን እንደሄደች እና ከሄደች ሁለት አመት እንደሆናት በመናገር የሀረግን መኖሪያ ገልፃለች።

በክፍል አስራ አራት፡-አባቡ እና ሰላም ከጓደኞቻቸው ጋር መሰብሰባቸውን ለመግለፅ የገባው የብዙ ሰው ጫጫታ አድማጭ በቤት ውስጥ ብዙ ሰው እንዳለ እንዲረዳ አድርጓል።

በክፍል ሃያ ሰባት፡-9:00 አማረ እና አባቡ ቁምሳጥን አምልጧቸው ሲወድቅ መውደቁ ያስደነገጠው የህንፃው ነዋሪ "ጉድ"፣"ልጆቻችንን"፣ የተለያዩ ሰዎች የቃል ምልልስ ቦታው የብዙ ሰው መኖሪያ ህንፃ መሆኑን ገልጿል።

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የሰው ድምፅ አጠቃቀም መቼትን ፣ገፀ ባህሪን ፣እና ታሪክን ከመግለፅ አንፃር ትልቁን ሚና ተጫውቷል።

3.4.3.3የሰው ድምፅ ከታሪክ አንፃር

ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ የገፀ ባህሪያትን ምልልስ ታሪኩን እንድንረዳ፣እንድናውቅ፣ታሪኩ ምን እንደሆነ፣ ገፀ ባህሪያት ምን እየሰሩ እንደሆነ፣በአጠቃላይ በታሪኩ ውስጥ እየተከናወነ ያለውን ነገር እንድንረዳ ከማድረግ አኳያ የሰው ድምፅ ትልቁን ድርሻ ይይዛል።ለምሳሌ

በክፍል አንድ፡-33፡18ላይ አማረ ከስራ መባረሩን የምናውቀው እራሱ አማረ በሚያደርገው ቃለ ተውኔት ነው።

በክፍል አስራ ሁለት፡-ፍሬ ገነት የተባለችው ገፀ ባህሪ ገንዘብ ለአቶ ተፈራ ማበደሯን ፍሬ ገነት አባቡ ለተባለው ገፀ ባህሪ ስትነግረው ነው የገንዘብ ማበደሯን ታሪክ የምንሰማው።

በክፍል አስራ ሶስት፡-ሞጃ ሰፈርን መልቀቃቸውን፣የገቡበትን ሰፈር ባለሀብት የሚበዛበት መሆኑን፣ገፀ ባህሪያት እርስ በእርስ በሚያደርጉት የቃል ምልልስ ሙሉ ታሪኩን ማወቅ ችለናል።

በክፍል ሃያ ስድስት፡-አዲስ የገቡበት ሰፈር እንዳልተመቻቸው እና ኮንደሚኒየም ሊገቡ እንደሆነ አማረ በሚያደርገው ቃለ ተውኔት መረዳት ችለናል።

በአጠቃላይ በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ ያሉ ቃለ ተውኔቶች ታሪኩን በሚገባ እንድንረዳው አግዘውናል።

በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የተጠቀሙት የሰው ድምፅ የተፈለገውን ድባብ ፈጥሯል?የሚለውን ስንመለከት በድራማ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያት ድምፃቸው ስሜታቸውን ቁጣን፣ደስታን፣ሳቅን፣ለቅሶን፣ ቀልድን፣መከፋትን፣ንዴትን፣የጎንዮሽ ንግግርን፣የርቀት ድምፅን፣የስልክ ምልልስን፣የብዙ ሰው ጫጫታን ሁሉንም በቦታው ያለን ያህል እስኪሰማን ድረስ ስሜታቸውን አጋርተውናል የተፈለገውን ድባብ ፈጥረዋል።ይህ ማለት በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ ተዋንያን የተጠቀሙት ድምፅ እጅግ ጥሩ ነበር ማለት ነው።ነገር ግን አንዳንድ ጉድለቶችም አይታዋለች።ምሳሌ፡-በክፍል አስራ ሶስት፡-29፡19 የሀረግ እና የአማረ የስልክ ምልልስ ለመግለፅ የተፈለገው የጀርመን እና የኢትዮጵያ የስልክ ልውውጥ ነበር።ነገር ግን የሀረግ ድምፅ ሀገር ውስጥ ሆና እንጂ ከባህር ማዶ የሚመጣ ድምፅ አይመስልም ነበር።የውጭ ሀገር ስልኮች ወደ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ድምፆች በመጠኑ የመዘግየት ባህሪ አላቸው።በዚህ የራዲዮ ድራማ የሰው ድምፅ አጠቃቀም ላይ ግን የሀረግ ድምፅ መዘግየትም፣መቆራረጥም ያልታየበት በመሆኑ የተፈለገውን ስሜት አልፈጠረም። ይህ የወፌ ቆመች ድምፅ አጠቃቀም ደካማ ጎን ነው።

ከወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማ ጠንካራ ጎኖች ምሳሌ ስንመለከት

ክፍል አንድ፡-13:42 አባቡ እና ሰላም ስልክ ሲነጋገሩ የስልክ ምልልሱ የስልክ ንግግር መሆኑን ገልጿል። **ክፍል አሰራ ሁለት፡-12:36** የሰላም ልደት ላይ የብዙ ሰዎች ድምፅ ከሙዚቃ እና ከብርጭቆ መጋጨት ጋር ሲደመር የሚፈለገውን ድባብ ፈጥሯል።

ክፍል ሃያሰባት፡-9:00 ቁምሳጥን ሲወድቅ የኮንደሚኒየም ነዋሪዎች ለማየት ወጥተው የሚነጋገሩት ንግግር የእውነት የወሬ ድባብ ፈጥሯል።

እነዚህ እንደ ምሳሌ ቢነሱም በወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማ ውስጥ የተጠቀሙት የሰው ድምፅ በተፈለገው መጠን ድራማውን አንቀሳቅሷል ።ወፈ ቆመች አዝናኝ እና አስቂኝ ይዘት ያለው ድራማ እንደመሆኑ ተዋናዮችም ድምፃቸውን በአግባቡ እና በተፈለገው መንገድ ስለተጠቀሙ እንደተፈለገው ድራማው አስቂኝ ይዘቱን ጠብቆ እዲቆይ የተዋንያን ድምፅ ዋናውን ሚና ተጫውቷል።

አጠቃላይ በወፈ ቆመች ላይ የነበረው የድምፅ አጠቃቀም ጥሩ በመሆኑ ድራማው ተወዳጅ ፣ግልፅ እና ግርታን የማይፈጥር እንዲሆን አድርጎታል።

3.5. ወፈ ቆመች የራዲዮ ድራማ ከዝምታ አንፃር

ዝምታ በራዲዮ ድራማ ውስጥ አንዱ አላባ ነው።ወፈ ቆመች ላይ ዝምታን ስንመለከት ድራማው አስቂኝ በመሆኑ ብዙም ልብ ሰቀላዎች (ዝምታ)የለውም ድርጊቶቹ ፈጠን ፈጠን ያሉ ናቸው።ነገር ግን አስፈላጊ ሆነው በተገኙ ጥቂት ቦታዎች ላይ ዝምታን ወይም ልብ ሰቀላን ተጠቅመዋል።ለምሳሌ፡-በክፍል አንድ **30:55** አማረ ቤታቸው ሊፈርስ እንደሆነ ደብዳቤ እንደደረሰው ሊነግራቸው ሲል ቃለ ተውኔት ቆሞ(ንግግር ላይ ፋታ ወስዶ)የገባው ክላሲካል ልብ ሰቀላን ለመፍጠር ነው።

በክፍል ሁለት፡-3:23 አማረ ቤት ለመስራት የጎደሉትን ነገሮች ብዛት ሊገልፅ ሲል የገባው ድምፅ ጉጉትን ለመፍጠር ነው።6:50 አማረ ለልጆቹ የስራ ክፍፍል ሲያደርግ ልጆቹ ምን ስራ እንደደረሳቸው ለማወቅ በጉጉት ላይ መሆናቸውን እና አድማጭም በጉጉት እንዲጠብቅ ለማድረግ የገባ ድምፅ ነው።18:51 ፍሬገነት እና የአማረ እናት ሊደባደቡ ሲሞክሩ በመካከላቸው ግጭት ይፈጠራል አይፈጠርም ሚለውን አድማጭ በጉጉት እንዲጠብቅ የገባ ድምፅ ነው።

በአጠቃላይ አጥኚዋ በወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ ወስጥ ያሉ አላባዊያን በዚህ መልኩ ተተንትነው ምንያህል የተፈለገውን ድባብ ፈጥረዋል፣ታሪክ፣ገፀ ባህሪና መቼትን በተፈለገው መንገድ መግለፅ አለመግለፃቸውን፣ ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን በዚህ መሰረት አስቀምጣለች።

ምዕራፍ አራት

4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ

4.1. ማጠቃለያ

የራዲዮ ድራማ አንድን ነገር በምስል ሳያሳይ በቃል ብቻ በአይን ያየን እስኪመስለን ድረስ ስሜትን ፈጥሮ የማቅረብ ጥበብ ነው።በራዲዮ ድራማ ውስጥ ተዋናዮችም ሆኑ አዘጋጁ ለአድማጭ የሚያቀርበውን ነገር ስለ እያንዳንዱ ነገር መጨነቅ እና ማሰብ አለበት።ምክንያቱም በሚያቀርበው ነገር ከአድማጭ ከሚያገኘው አድናቆት እና እውቅና በዘለለ ለሙያው ትርጉም መስጠት እና መተግበር ስላለበት ስለሚሰራው ነገር በሚገባ ማሰብ አለበት።ወፌ ቆመች ተሰኘው የራዲዮ ድራማ ከተዋናዮች፣ከአቀራረብ፣ከአላባዊያን አጠቃቀም አንፃር እጅግ በጣም ጥሩ የሚባል ነው።ድራማውን ጥሩ ሊያስብሉት የቻሉ ነገሮች ለራዲዮ ድራማው አስፈላጊ ተብለው የተቀመጡ አላባዊያንን በተገቢው በመጠቀሙ እና ለመፍጠር የተፈለገውን ምስል በሰው አህምሮ ውስጥ መፍጠር በመቻሉ ነው።ነገር ግን አላባዊያን አጠቃቀም ላይ አንዳንድ ክፍተቶችም አይጠፉም።ቢሆንም ወፌ ቆመች የራዲዮ ድራማ የሚጠበቅበትን ማሳየት የቻለ ጠንካራ ጎኖቹ ጎልተው ከክፍተቶቹ በልጠው የሚታዩበት አዝናኝ የራዲዮ ድራማ ነው።

በአጠቃላይ ድራማው ከራዲዮ ድራማ አላባዊያን አንፃር ተተንትኖ ጥቂት ክፍተቶች ቢታዩበትም በጥሩ የራዲዮ ድራማ ምሳሌነት መቅረብ ይችላል።አጥኚዋ በራዲዮ ድራማው ላይ ያስተዋለችውን እና ክፍተት ነው ብላ ያመነችበትን ሃሳብ እንደሚከተለው አስቀምጣለች።

የታሪክ ክፍተት

ሰላም ከአዲሱ ቤታቸው በጠፋች የሰፈሩን ስም አታውቅም፣ GPS አታውቅም ግን ከጠፋችበት ቴዲ ያገኛታል እንዴት ሊያገኛት እንደቻለ አልተገለፀም።እንዴት?የሚል ጥያቄ ፈጥሯል።ታሪኩን ለመጨረስ የተደረገ ጥድፊያ ነው።

አማረ ቤት ለመልቀቅ የተሰጠው የሁለት ሳምንት ቆይታ ነበር።ይህ ደብዳቤ ሲደርሰው እየሰራ የነበረው ቤት ገና መሰረት የወጣለት ግድግዳ ብቻ ነበር።ከሁለት ሳምንት በኃላ ግን ሙሉ ጣሪያ የለበሰ የተስተካከለ ቤት ውስጥ የገባሉ።ይህ ደሞ በመጀመሪያ አማረ ከስራ የተባረረ ሰው ነው በፍጥነት ቤቱን ለመስራት ገንዘብ ከየት አመጣ?ሲቀጥል በሁለት ሳምንት ውስጥ እንዴት ቤት ይሰራል?የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል።

ከእውነታው ትንሽ የሸሸ ነው።ይህ ታሪኩን በግዴለሽነት የታለፉ ቦታዎች እንዳሉ ግልፅ ሳይደረጉ ለመጨረስ ብቻ የተደረገ ነው።ይህ በድራማው ላይ የታየ ችግር ነው።

ተመላሽ የሚለው ክፍል ላይ ሀረግ መዘረፉዋን ከነገሩን በኃላ መልሰው በኢንተርኔት እና GPS በመጠቀም ቤተሰቧን ማፈላለግ ጀመረች ይላል።በምን?ከተዘረፈች ስልክም ገንዘብም ከሌላት በምን ነበር ኢንተርኔት ትጠቀም የነበረው?አጥኚዋ ይህም ክፍተት ሆኖ አግኝታዋለች።

የገፀ ባህሪ ክፍተት

ቤቢ ተብሎ የተሳለው ገፀ ባህሪ ጉልበተኛ፣ሰፈር አሸባሪ ተደርጎ ነበር ነገር ግን ይህን ገፀ ባህሪ የወከለው ተዋናይ ከድምፁ፣ከአነጋገሩ(ቃለ ተውኔት) አጠቃቀሙ አንፃር ስንመለከተው የተሳለው ገፀ ባህሪ ማምጣት አልቻለም።ከዚያ በተቃራኒ ሞኝ ወይም ጅል የምንለውን አይነት ባህሪ የወከለ እስኪመስል መጀመሪያ የተሳለውን ገፀ ባህሪ ማምጣት አልቻለም።አዘጋጇ ይህን ክፍተት ተዋናዩ ላይ በደንብ ልምምድ መስራት ብትችል አልያም ተዋናዩን መቀየር ቢቻል የተፈለገውን (የተሳለውን) ገፀ ባህሪ አድማጭ ጋር ማድረስ ይቻል ነበር።

ሀረግ የተጫወተችው ተዋናይ እና ሰላምን የተጫወተችው ተዋናይ እናት እና ልጅ ተደርገው ነው በድራማ ውስጥ የተሳሉት ነገር ግን አዘጋጇ የተጠቀመቻቸው ተዋንያን ድምፅ ተቀያይሮ ነበር።የሐረግን(እናት) ገፀ ባህሪ የተጫወተችው ተዋናይ ድምፅ ሰላምን(ልጅ)ሆና ከተጫወተችው ተዋናይ በይበልጥ የልጅ ድምፅ ይመስል ነበር።አዘጋጇ ይህን በማስተዋል ተዋንያኑ የሚጫወቱትን ሚና የገፀ ባህሪ ልውውጥ (ቅይይር) ማድረግ ቢቻል የገፀ ባህሪያቱን ማንነት በተሻለ መልኩ ለአድማጮች ምስል መፍጠር ይችል ነበር ።

የመቼት ክፍተት

የሞጆ ሰፈር ሲፈርስ የሰፈሩ ነዋሪ የመሰነባበቻ ፕሮግራም የአዘጋጀበት ቦታ ሰፈር ውስጥ ድንኳን በመትከል ነበር ለመሰብሰብ የመከሩት ነገር ግን የተሰበሰቡበት ቦታ የሚያስተጋባ በመሆኑ የአዳራሽ ድባብ እንጅ የድንኳን ወይም ከቤት ውጭ ያለን ቦታ ድባብ ሊፈጥር የሚችል አልነበረም።

አጥኚዋ በጥናቱ ላይ የመፍትሄ ሀሳብ ብላ ያቀረበችውን ሀሳብ በዚህ መልኩ አስቀምጣለች።የተጣረሱ አድማጭ ላይ ጥያቄ የሚያስነሱ ሃሳቦች እንዳይኖሩ መጠንቀቅ እና አዘጋጆች ስለሚሰሩት ስራ ትኩረት መስጠት ቢችሉ በይበልጥ የተሻለ ስራ መስራት እና የኢትዮጵያን የጥበብ ኢንዲስትሪ ከፍ ማድረግ ይቻላል።በድራማው ላይ እንደ ክፍተት የተነሱ ሀሳቦች ቢቀረፉ የድራማው ውበት እና ተወዳጅነት ይጨምራል ለማለት ያስችላል።

4.2 የመፍትሔ ሀሳብ

ይህ ጥናት በጥናቱ ላይ የተገኘውን ግኝት በመመርኮዝ የመፍትሔ ሀሳቡን ይዳስሳል።ወፈ ቆመች ያንያህል ብዙ ጉድለቶች ባይኖሩትም ያሉትን ስህተቶች ለማስተካከል እና ከዚህ የተሻለ ስራ ለማቅረብ አጥኚዋ የመፍትሄ ሀሳብን አቅርባለች።አጥኚዋ በጥናቱ ላይ የመፍትሄ ሀሳብ ብላ ያቀረበችውን ሀሳብ በዚህ መልኩ አስቀምጣለች።የተጣረሱ አድማጭ ላይ ጥያቄ የሚያስነሱ ሃሳቦች እንዳይኖሩ መጠንቀቅ እና አዘጋጆች ስለሚሰሩት ስራ ትኩረት መስጠት ቢችሉ በይበልጥ የተሻለ ስራ መስራት እና የኢትዮጵያን የጥበብ ኢንዲስትሪ ከፍ ማድረግ ይቻላል።በድራማው ላይ እንደ ክፍተት የተነሱ ሀሳቦች ቢቀረፉ የድራማው ውበት እና ተወዳጅነት ይጨምራል ለማለት ያስችላል።

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1) The word Radio is defined as the process of sending and receiving messages through the air, using electromagnetic waves.

2) The history of radio dates back to the 19th century when Samuel Morse invented the electric telegraph. According to Bittner(1989:93)Gugielmo Marconi built on this invention to produce electromagenetic impulses which would be sent though the air without the use of wires. The voice was carried over long distances.Thus,1866, signals were transmitted from England to America without eires. In 1988 Heinric Hertz,Working on the electromagnetic theory propunded earlier by a British scientist James Clark Maxwell,produced the first radio waves.

3)At the very last ,the absence of vision imposes huge restrictions an the kinds of play radio can do large cast dramas are next to impossible in any one scene the listener can accomodete at best only four or five major speaking character with distinictive voices.

4)The plot must not be too obvious;there must be conflict,a struggle between characters or between characters and situation The climax may be unexpected indded,the listener is pleased by the surprise ending.

5) The dramatic writer for radio uses various devices to creat moods and effects to economize in time.

6) The narrator's introductin is decidedly important,for the must set the stage for the listener.

7) If we do not take care of our voice and the way we speak,we will not make it easy for the listener to understand our message.speak slowly,move your mouth and do not laugh.

8) Music is very important. its main aim is to generate the appropriate atmosphere so as to make language work on the listener and with the desired objective.

9) Silence is very useful resource to put emphasis and atmosphere to the radio message.

10) Sound effect ,which are nither word nor music,noises and effects provoke the listener to imagine. Thus they are important in radio message.

ዋቢ መፅሃፍት

ሳሙኤል ተስፋዬ።የመድረክ ጀርባ ጥበባት።አዲስ አበባ፣ማይቢቲ ማተሚያ ቤት፣2012።

አለም እሸቱ።መሰረታዊ የምርምርና ዘገባ አፃፃፍ።የቅድስተ ማርያም ኮሌጅ ሬጉላር አርትስ ፋክሊቲ ህትመት።1994።

አስታጥቃቸው ይሁን።የመማሪያ ሞጁል።አዲስ አበባ።1998።

ዘሪሁን አስፋው።የስነፅሁፍ መሰረታዊያን።አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣2005።

የሻው ተሰማ ።የተውኔትአፅናፍመነፅር።አዲስአበባ፣ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ፣1998ዓ.ም ።

ያለው እንዳወቀ ሙሉ።የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣2009።

ፋንታሁን እንግዳ።ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ።አዲስ አበባ፣ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣1993።

_____።የተዉኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ።አዲስ አበባ፣ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣2005

ሃይለማርያም ሰይፉ፣ላዕከማርያም ልሳነወርቅ፣ሳሙኤል ተስፋዬ።።።የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር የጥናትና ምርምር ጆርናል።አዲስ አበባ።2009

ጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ፣ተስፋዬ ገ/ማርያም፣አስታጥቃቸው ይሁን፣እቴነሽ ካሳ፣ዐለማየሁ ታደሰ።መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መርሆች።አዲስ አበባ።2009።

Oberiri Destiny Apuke.Introduction to Radio Production.Nigeria. 2017

Ruben Bermejo.The Elements Of Radio.2017

Waldo Abbot.Handbook of Broad casting. New work,1957.